# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያቋንቋዎችእና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን ማስተማር ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በደነባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በየምሳ አፍ ፊት የ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ፍቃዱ ኦላኒ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2015

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችእና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን ማስተማር ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በደነባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በየምሳ አፍ ፊት የ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ፍቃዱአላኒ

አማካሪ፡ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ የሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2015

ኢትዮጵያ ጅማ

## ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንባብን ማስተማር ለየምሳ አፍ ፈት ተማሪዎች ለአንብቦ የመረዳት ክሂል መዳበር ያለው አስተዋፅኦ፣ በደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት በፍቃዱ ኦላኒ የቀረበን ጥናታዊ ሥራ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፊርማችን ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

-አማካሪ________________________________ ፊርማ ____________ ቀን ____________

-የውጭ ፈታኝ__________________________ ፊርማ______________ ቀን_____________

-የውስጥ ፈታኝ__________________________ ፊርማ______________ ቀን ____________

## የአጥኚው ማረጋገጫ

የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን ማስተማር ለየምሳ አፍ ፈት ተማሪዎች ለአንብቦ የመረዳት ክሂል መዳበር ያለው አስተዋፅኦ፣ በደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ እና ሂማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናታዊ ሥራ ለመሥራት በርካታ ምንጮችን የተጠቀምኩ ሲሆን እነዚህን ምንጮችም በአግባቡ በዋቢ ውስጥ ጠቅሻለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ሥራ የራሴና ወጥ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ________________________

ፊርማ ______________________

ቀን ________________________

## ም ስጋና

በቅድሚያበነገሮችሁሉለረዳኝለልዑልእግዚአብሔርክብርምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠል ጥናቱ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ለስኬት እንዲበቃ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፣ ስህተቴን በማረም፣ ለስራዬ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ለጊዜያቸውና ለጉልበታቸው ሳይሳሱ ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ የማማከር እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ለማ ንጋቱ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በተጨማሪም ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ ረዳት አማካሪዬ ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ለስራዬ መሳካት የሀሳብ ድጋፍ ላደረጉልኝ ከጎኔ ላልተለዩኝእናቴ ወ/ሮ ቡሌ ጣልቦ እና ለባለቤቴ መ/ርትጌጤ ንጉሤ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት የተሳካ እንዲሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ፈተናዎችንበማረም፣አስተያየቶችንበመስጠትሙያዊእገዛቸውላልተለየኝለደነባ አጠቃላይሁለተኛደረጃትምህርትቤትየአማርኛቋንቋመምህራንእናለጥናቱመረጃበመስጠትየ ተባበሩኝንየደነባ

አጠቃላይሁለተኛደረጃትምህርትቤትየአሥረኛክፍልተማሪዎችንከልብአመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


የአጥኚው ማረጋገጫ ....... i

ምስጋና ....... i

ማውጫ ....... ii

የሠንጠረዥማውጫ ....... iv

አጠቃሎ ....... v

ምዕራፍ አንድ ....... 1

መግቢያ ....... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 5

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ....... 7

1.4 የጥናቱ ዓላማ ....... 7

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 7

1.6 የጥናቱ ወሰን ....... 8

ምዕራፍ ሁለት ....... 9

ክለሳ ድርሳናት ....... 9

2.1 የማጠቃለል ብልሀት ምንነት ....... 9

2.1.1 በማጠቃለል ብልሀት ማንበብን ማስተማር የአንብቦ መረዳትን ክሂል ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ ....... 10

2.1.2 በማጠቃለል ብልሀት አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የተማሪዎች ባህሪያት ያላቸው ተፅዕኖ ....... 11

2.1.3 የማንበብና አንብቦ የመረዳትምንነት ....... 13

2.1.3.1 የማንበብምንነት ....... 13

2.1.3.2 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምንነት ....... 15

2.1.3.3 የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች ....... 17

2.1.3.4 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ....... 19

2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....... 21

ምዕራፍ ሦስት ....... 25

የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ....... 25

3.1 የጥናቱ ንድፍ ....... 25

3.2 የናሙና አመራረጥ ....... 26

3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ....... 26

3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ....... 26

3.2.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 26
3.2.4 የምድብ (ሴክሽን) እና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 26
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 27
3.3.1 ፈተና ........ 27
3.3.2 ቃለ መጠይቅ ........ 28
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 28
3.5 የጥናቱ ሂደት ........ 29
ምዕራፍ አራት ........ 30
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 30
4.1 የመረጃ ትንተና ........ 30
4.2 የፈተና መረጃ ትንተና ........ 30
4.3. የቃለ መጠይቅ መረጃ ትንተና ........ 37
4.4 የውጤት ማብራሪያ ........ 38
ምዕራፍ አምስት ........ 43
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........ 43
5.1 ማጠቃለያ ........ 43
5.2 መደምደሚያ ........ 44
5.3 አስተያየት ........ 45
ዋቢ ጽሁፎች ........ 46
አባሪ "1"፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ........ 49
አባሪ "2"፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ........ 52
አባሪ "3"፡- የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ........ 55
አባሪ "4"፡- የማስተማሪያ ጽሁፎች ........ 56
አባሪ "5"፡- የቅድመ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት ........ 70
አባሪ "6"፡- የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት ........ 71
አባሪ "7"፡- የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት ........ 72

## የሠንጠረዥ ማውጫ

**ሠንጠረዥ** 4.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ……………31
**ሠንጠረዥ** 4.2 የሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ልኬት………………………………………………………………………………31
**ሠንጠረዥ** 4.3 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭ ስታትስቲክስ…………………………………………..32
**ሠንጠረዥ** 4.4 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት…………...........................................................................33
**ሠንጠረዥ** 4.5 የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭ ስታትስቲክስ…………………………………………………34
**ሠንጠረዥ** 4.6 የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና በዳግም ልኬት ናሙና ተ-ቴስት………...........................................................................…35
**ሠንጠረዥ** 4.7 የሙከራዊ ቡድንና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና በነፃ ናሙና ገላጭ ስታትስቲክስ………………………………………...…35
**ሠንጠረዥ** 4.8 የሙከራዊ ቡድንና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ልኬት ……….........................................................……………36

## አጠቃሎ

የዚህጥናትዋናዓላማየማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን ማስተማር ለየምሳ አፍ ፊት ተማሪዎችአንብቦ የመረዳት ክሂልመዳበር ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው፡፡ አላማውን ከግብ ለማድረስ ከፊል ሙከራዊ የምርምር ንድፍ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን በማስተማር እና የማንበብን ክሂልን በተለመደው ዘዴ በማስተማር ሁለቱን ቡድኖች ተማሪዎችንበቁጥጥርና በሙከራ ቡድን በመመደብ ለአራት ሳምንታት እንዲማሩ ተደረጓል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ካሉ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በታላሚ ንሞና የተመረጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከተሳታፊዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን ለመመዘን በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና መረጃ ተሰብስቧል፡፡ መረጃዎችም በአማካይ ውጤት፣ በመደበኛ ልይይት፣ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት በገለፃና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነው የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡ የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት 45.91 ከቁጥጥር ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት 45.03 በ0.88 በልጦ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት 0.41 ከቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት 0.29 በ0.12 አንሶ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የሁለቱም ቡድኖች ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤት ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት አለው ማለት ይቻላል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በመጠቀም የተሰላው የሁለቱ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘው ውጤት (ቲ(110.926) = -8.949፣ P = 0.001) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የ"P" ዋጋ ከተቆረጠለት $P < 0.05$ ያነሰ በመሆኑ የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች የማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማንበብን በማስተማር ምክንያት አንብቦ የመረዳት ክሂልችሎታቸው ላይ የውጤት መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ስለዚህ መምህራን የማጠቃለልን ብልሀት ቢጠቀሙ የተሻለነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረትያደርገው በደነባ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማጠቃለል ብልሀትለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ የየምሳ አፍ ፊት ተማሪዎችን በመጠቀም በመፈተሽ ላይ ነው፡፡የጥናቱ ዋና ዓላማየማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ክፍሎችም በአምስት ምዕራፍ የተከፈለ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ፡- የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሪ ጥያቄ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን የያዘ ሲሆን፤ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የፅንሰ ሀሣብ መነሻንድፈ ሀሳብእና የተዛማጅ ጥናትንያካትታል፤ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ተሳታፊዎችና የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የጥናቱ ሂደትና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ሲሆን በምዕራፍ አራት ደግሞ የመረጃ ትንተና በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት የጥናት ውጤት ትንተና እና አስተያየት አካቷል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሌሎች የቋንቋ የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ የራሱ የሆኑ አላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም ዓላማዎች መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎችን (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) ማዳበር እና የስነ ልሳንና የስነ ፅሁፍ ዕውቀቶችን ማስጨበጥ ናቸው፡፡ ስለሆነም አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱት ይዘቶች ልዩ ትኩረትን ይሻሉ፡፡ አንብቦ መረዳት አንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት እንደ መሆኑ የቋንቋ ትምህርትን አላማ ያሳካ ዘንድ ተገቢ ይዘቶችን እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ እንዲሁም ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመግባባት ተግባር የሚያጎለብት እንዲሆን ይጠበቅበታል፡፡

Grellet (1981) በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉም ክሂሎች እንዲዳብሩ ይፈለጋል፡፡ ከአራቱ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ የሆነው የማንበብ ክሂልን ለማዳበር መምህራን በይበልጥ በአጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን አቅም ለመለካት በተለያዩ የትምህርት አይነቶች የሚዘጋጁ ፈተናዎች በዋናነት የንባብ ግንዛቤ አቅምን ይጠይቃሉ፡፡ የቀለም ትምህርትን ከመረዳት ባለፈ ክሂሉ ለተማሪዎች ከትምህርታቸው ውጭ ከተለያዩ ጽሑፎች ጋር ጥሩ የሆነ ተግባቦት እንዲፈጥሩ ያግዛል፡፡

እንደ Carrell (1988) አገላለጽ ደግሞ ማንበብ በበርካታና ሰፊ ጽሁፍ ውስጥ ፀሐፊው ለፊደላትና ለቃላት፣ ለሐረጋትና ለዓረፍተ ነገሮች የተጠቀመውን የትርጉም አሰጣጥ የምንገነዘብበት ሂደት ነው ይላል፡፡ Edaso (2007)፣ Biges,Entewen and Kirban (1988)ን ጥናቶች ጠቅሶ እንዳሰፈረው ማንበብ ከጽሑፎች መረጃ የማሰባሰብ ሂደት ነው፡፡ የመረጃ ሂደቱም ቅደም ተከተልን ያላቸው ስምንት ደረጃዎችን የጠበቀ መረጃን የማሰባሰብ ሲሆን የፊደል ቅርጽን፣ ፊደላትን፣ ድምፆችን፣ ቃላትን፣ የቃላትን ትርጉም፣ ጽንሰሀሳቦችን፣ ዋና ሀሳቦችን እና ጭብጦችን ያካትታል፡፡ በኢዳሶ አባባልም የፊደል ቅርጽንፊደላቱ የተመሰረቱበት መስመር፣ ፊደላትየቅርፆች አመሰራረት ቅጣምባር፣ ድምፆችፊደላት የሚሰጡትን ድምጽ፣ ቃላትፊደላት በአንድ ላይ ሆነው የሚሰጡት ድምጽ ትርጉም፣ የቃላት ትርጉም ቃላቱ የሚሰጡት አንድ ትርጉም ወይም አባባሎች ቀለል ያሉ መሆን አለባቸው፡፡

አንብቦ መረዳት የትርጓሜ ትውስታዎችን የምናከናውንበት መሆኑን፣ ጽንሰ ሀሳቦችቀጥተኛ ባይሆንም የጽሁፉን ሀሳብ መረዳት፣ ዋና ሀሳቦችንየጽሁፉን ወካይ የሆነውን ሀሳብ ወይም ጠቅለል አድርጎ የያዘው ነጥብ መሆኑንና ሃሳቦችና ዋና ሀሳቦች የትርጓሜ ፈጠራው አካሎች መሆናቸውን Kirby 1988 አብራርቷል፡፡ በተመሳሳይ ጭብጥበጽሁፍ ውስጥ ምን ለማለት እንደተፈለገ የትርጓሜ ሥራ የሚከወንበት መሆኑ ተገልጧል፡፡

እንደ Tesfu (2015)፣ አገላለጽ ደግሞ ማንበብ በሁለት የተያያዙ ሂደቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን የቃላት ግንዛቤና አንብቦ መረዳት ናቸው፡፡ የቃላት አውቅና ወይም ግንዛቤ የተጻፉት ምልክቶች አንድ ሰው ከሚናገረው ቋንቋ ጋር ያላቸው የስርጸት ሂደት ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ደግሞ በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም መረዳት መሆኑን ጠቅሷል፡፡

Grellet (1981)፣አንብቦ መረዳት በጣም አስፈላጊ የሆነ የቋንቋ መማሪያ ንዑስ ክሂል ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ለተማሪዎቻችን በአግባቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ብቃትና ችሎታ፣ ለትምህርታቸው ስኬታማነት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ብቃት ወይም ችሎታ ደግሞ የጽሁፉን ዋና ሀሳብ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን ያልተለመዱ ቃላትን ትርጉም ወይም አባባሎች፣ ማጣቀሻዎች ማሰባሰብን፣ የፀሐፊውን ዓላማ መረዳትንና ዕሁፉን መገምገምን የሚያካትት መሆኑን ዘርዝሯል፡፡

እንደ USAID (2016)፣ አንብቦ መረዳት ማለት ከቴክስት ትርጉም የማውጣት ንቃተ ህሊና ሂደት እና አንባቢ ከጽሁፍ ትርጉም የሚያወጣበት ሂደት ነው፡፡ በዚህም ሁለት ዓይነት የመረዳት ክሂሎች አሉ፡፡ እነሱም ቀጥተኛና አንድምታዊ ይባላሉ፤ ቀጥተኛ መረዳት ማለት በጽሑፉ በቀጥታ የተገለጸን ሀሳብ ማወቅ ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሀቅን ወይም እውነታን የማስታወስ ወይም መሰረታዊ ግንዛቤ የማግኘት ችሎታ የሚጠይቀው ቀላል ክሂልን ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድምታዊ መረዳት ከተባለው በመነሳት ያልተባለውን ማውጣት ወይም በአንድምታ ለመረዳት የቋንቋ እውቀትን መጠቀም ማለት ነው፡፡

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች፣ Pardo (2004)፣ ገለጻ መሰረት ጥሩ አንባቢያን ጽሁፎችን የሚያገናዝቡበት አእምሯዊ ሂደት ነው፡፡ እነዚህንም ብልሀቶች ለአንባቢዎች በግልጽ በማስተማር ጽሁፎችን ትርጉም ሰጥተው እንዲያነቡ ማድረግ ይፈለጋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ሂደቱ ንባብ ከመጀመር በፊት የሚጀምርና ከንባብ በኋላም የሚቀጥል ነው፡፡ ጥሩ አንባቢያን የቅድመ-ንባብ አሰሳዎችንና ከንባብ በኋላ ያሉ ማጠቃለሎች ጨምሮ በርካታ ብልሀቶችን በንባብ ጊዜ ይጠቀማሉ፡፡ Harvey and Goudvis (2000)፣ እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች፣ ቅድመ ዕውቀትን ማነቃቃት፣ መከታተልና ግልፅ ማድረግ፣ መተንበይ/መገመት/፣ ጥያቄዎችንና ማጠቃለያዎችን ማዘጋጀት የሚሉትን ዘርዝረዋል፡፡

Edaso Mulu (2007)፣ Encychlopidia (1992)፣ Langan (2003)፣ Nuttall (1982)፣ Anadorkin (1974)ን ጠቅሶ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ውስጥ አንባቢዎች ከማያውቁት ቃል በፊትና ቀጥሎ ያሉ ፍንጭ ሰጪ አባባሎችን በመጠቀም፣ የቃላትን ሰዋሰዋዊ አገባብ በመጠቀም፣ የቃላትን ቅድመ ቅጥያ፣ ድህረ ቅጥያ እና ዋና ግስ በመጠቀም አንብቦ መረዳትን ማዳበር እንደሚቻል አብራርቷል፡፡

ማጠቃለል ማለት ዋናውን ጽሁፍ በማሳጠር በጣም አስፈላጊ ነጥቦችን፣ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ አስፈላጊ ዝርዝሮችን ብቻ የያዘ ከዋናው ጽሁፍ ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነን ጽሁፍ ማደራጀት ነው፡፡ በማጠቃለል አላስፈላጊ መረጃዎችን በማስወጣትና አጠቃላይ ሀሳብን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር መሆኑን Denton and etal (2007)፣ ገልፀዋል፡፡ በDentonን አገላለጽ ስድስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡- ዋና ዋና ሀሳቦችን ማስፈር፣ አስፈላጊ ነጥቦችን ማስመር፣ የሚቻሉትን ማያያዝ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ማጠቃለያውን መጻፍና ማጠቃለያውን መከለስ/ማሻሻል ናቸው፡፡

አንድን በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍን በማንበብ ሀሳቡን በታመቀና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል ሲል Oxford (1990)፣ አብራርተዋል፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመነሻ ጽሁፉን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግን ይፈልጋል፡፡

አንድን ጽሁፍ ለማጠቃለል፣ የማጠቃለል ብልሀትን በመጠቀም ተማሪን ማለማመድ እንደሚቻል Armbruister and etal (2002)፣ ጠቁመዋል፡፡ ከስልቶች ውስጥ የጽሁፉን መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይ ሀሳቡን የሚያመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን ማስፈር በመሪ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር የሚካተቱ ሀሳቦችን መለየት፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀት እርከናዊ አጠቃሎ (Hierarchical summary) Tayler and Bich (1984)ን፣ Tayler and Berkoywites (1980)ን፣ በመጥቀስArmbruister and etal (2002)፣ አስረድተዋል፡፡ በዚህም ርዕሶቹን፣ ንዑስ ርዕሶቹን እና አንቀፆቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ማዘጋጀት፣ በመቀጠልም በየርዕሶቹ፣ በየንዑስ ርዕሶቹና በየአንቀፆቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይቶ ማውጣት፡፡ በመጨረሻሻም ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሳብን በማፍለቅ በመሪው ሀሣብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሳብ መጻፍ የሚሉ ናቸው፡፡ Birawon and Diay (1983)፣ Rahert (1986)ን ዋቢ በማድረግ Armbruister and etal (2002)፣ እንደጠቀሱት አላስፈላጊ መረጃዎችን፣ የተደጋገሙ መረጃዎች ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመተካት ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ የተገለፁ ሀይለ ቃሎች ወይም ዋና ሀሳቦች ካሉ እንደ መሪ ሀሳብ አድርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀፁን ዋና ሀሳብ በሀይለ ቃል መልኩ ያላሰፈረ ከሆነ በአንባቢው በኩል የራስን ሀይለ ቃል መፍጠር ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን የምሁራን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ፤ አጥኚው በሀገር ውስጥ ማለትም በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት የየምሳ ተማሪዎችን በሁለት ከተነሱት ጎራዎች አንፃር የማጠቃለል ብልሀት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አስፈላጊ ነው ወይም አስፈላጊ አይደለም የሚሉትን የተሰነዘሩሀሳቦች በመፈተሽ በተማሪዎች የአንብቦመረዳት ላይ የማጠቃለል ብልሀት ምን ይመስላል የሚለውን ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በዚህ ጥናት ለመዳሰስ የተሞከረው ዋና ጉዳይ የየምሳ አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ መረዳትንበማጠቃለል ብልሀት በማስተማር ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው መረጃዎችን ከመዳሰስና ካለው የማስተማር ልምድ አንጻር ያጋጠሙትን መነሻ ምክንያቶች ለማየት ሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው አነሳሽ ምክንያት ለተለያየ የክፍል ደረጃ ማስተማሪያነት ተዘጋጅተው በስራ ላይ የዋሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ባሉት ሁሉም ምንባቦች እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ የማጠቃለል ብልሀትን ተማሪዎች በተለያዩ አግባቦች እንዲመልሱ ያዛሉ፡፡ ነገር ግን አጥኚው እስካሁን በመምህርነት እና በሱፐርቫይዘርነት በሰራባቸው ትምህርት ቤቶች ብዙ መምህራን ሲጠቀሙበት አልተመለከተም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተደረጉ ጥናቶችን በሚዳስስበት ጊዜተቀራራቢ የሆኑ ማለትም ማንበብን በተለያየ ዘዴ ሲቀርብ ለአንብቦ መረዳት ያለውንአስተዋፆ አስመልክቶ ብዙ ምሁራን አጥንተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ገብረመድን ተስፋው (2011)፣ ታምሩ ፀጋዬ (2008) እና ከድር ሰይድ (2009) ይገኙበታል፡፡ ነገር ግን የማጠቃለልን ብልሀት ተጠቅሞ ማንበብን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና በሚል፣ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተሰራ ጥናት ለማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡ ተቀራራቢ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ይህን ጥናት ለማጥናት ይሞከራል፡፡ ይኸውም፡-

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጠቃለል ብልሀቶች ትምህርት በመታገዝ ማጎልበት አስፈላጊ መሆኑ ይገለጽ እንጂ Langer and Mulasie (1988)ን፣ በመጥቀስ Conley (1992) እንዳሰፈሩት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ተፈላጊ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ይቀራል፡፡ ለዚህም እንደአንድ ችግር የሚጠቀሰው መምህራን ክሂሉን ሲያስተምሩ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በተገቢው መንገድ አለማለማመዳቸው ይመስላል፡፡ ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክረው Notum (1997)፣ የጥናት ውጤቶች የሚያሳዩት በአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ውስጥ ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሞዴል ማድረግና መግለጽ ወይም ማብራራት ችላ መባላቸውን እንደሆነ በመግለጽ በማስተማር ሂደቱ ዙሪያ ችግር መኖሩን መጠቆማቸው ነው፡፡

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በመማር አስፈላጊነት ዙሪያ የሚስማሙ ተመራማሪዎች ቢኖሩም ብልሀቶችን በማስተማሪያ መንገዶች ላይ ግን የተለያዩ ሀሳብ አላቸው፡፡በተለይም ብልሀቶችን በግልጽ በማስተማርና ባለማስተማር መካከል የተለያየ

ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ይስተዋላሉ፡፡ ለአብነትም Brown and Others (1986)፣ Plisar and Brown (1984)፣ Wnstien and Mayer (1986)፣Winglande and Haline (1988)በመጥቀስ O'Malley and Chamot (1990) እንደገለፁት ተመራማሪዎቹ የመማር ብልሀቶቹን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በግልፅ ማስተማር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

አጥኚው ከዚህ በላይ የተነሳውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በሀገር ውስጥ ማለትም በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፊት የሆኑ የየምሳ 10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከላይ ከተሰነዘሩት ሀሳቦች ወይም በሁለት ከተነሱት ጎራዎች አንፃር የማጠቃለል ብልሀት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አስፈላጊ ነው ወይም አስፈላጊ አይደለም የሚለውን የተሰነዘረ ሀሳብ በመፈተሽ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ላይ የማጠቃለል ብልሀት ምን ይመስላል የሚለውን ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው የዚህ ጥናት አጥኚ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማረባቸው ረጅም አመታት ከተለያዩ ትምህርት ቤት የቋንቋ መምህራን ጋርለመወያየት ባገኘው ዕድል ብዙ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸው መረዳት ችሏል፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትምህርት አሰጣጡ ተማሪ ተኮር ወይም አሳታፊ የትምህርት አሰጣጥ እየተበረታታ በመምጣቱ ብዙ የአማርኛ መምህራን ለተማሪዎች ማስታወሻአዘጋጅተው በመፃፍ ላይ አያተኩሩም ወይም ማስታወሻ አይሰጡም፡፡ ከዚህ ይልቅ በራሳቸው ተማሪዎች የመማሪያ መፃህፍትን እያነበቡ ከየምንባቦች የተረዱትን ፍሬ ሀሳብ በደብተር እንዲያሰፍሩ፣ ማጠቃለያዎችንና ማስታወሻ እንዲፅፉ ይደረጋል፡፡ይህም አንዱ ተግባራቸው እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ይህን ለማድረግ ሲቸገሩ ይታያል፡፡የማስታወሻ ደብተር የሌላቸው በርካታ ናቸው፤ መምህር ሲያስተምርም ማስታወሻ አይዙም፤ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው፤ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ ስለምንባቡ የተጠቃለለ ሀሳብ የማቅረብ ችግር አለባቸው፤ ብሎም ችሎታ ካላቸው ከተወሰኑ ተማሪዎች ደብተር እየተዋሱ ሲገለብጡ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ከሌሎች ሲገለብጡ ከነስህተቶች በመገልበጥ የተዛባ አረዳድ ይታይባቸዋል፡፡ አንዳንዶችም ችሎታው የሌላቸውና የሚዋሱት ያጡ ምንም ዓይነት ማስታወሻዎች የሌላቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተጠቀሰው እንደ አጥኚው ዳሰሳ፣ የማጠቃለል ብልሀትን መማር አስፈላጊነት የሚስማሙ ተመራማሪዎች Lunzer and Gardner (1979)፣ እንዳሉ ሁሉ በዚህ ሀሳብ የማይስማሙ ተመራማሪዎች Doll and Others (1991)፣ መኖራቸውን በመገንዘብ የብልሀቱን መማርና ስኬታማነት ከባህል ባህል መለያየቱ ከሀገራችን አውድ

አንጻር መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑ፣ የማጠቃለልአንብቦ መረዳት ብልሀትን መማርና አለመማር ከተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና በመፈተሽ በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱ ሁነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነዚህንም ችግሮች በጥናቱ ለመፈተሽ ጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይመስላል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

- የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን ይመስላል?
- የማጠቃለል ብልሀትን በግልፅ በመማርና ባለመማር መካከል ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ጉልህ ልዩነት ይኖረዋልን?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የማጠቃለል ብልሀት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚከተሉትዝርዝር ዓላማዎች ቀርበዋል፡፡

- የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና መመርመር፣
- ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀትን ከመማራቸው በፍትና ከተማሩ በኃላ አንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ ለውጥ መኖር አለመኖሩን መፈተሽ
- በሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ከላይ ለቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ለተማሪዎች፣ ለቋንቋ መምህራን እና ለተመራማሪዎች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ከማስገኘት አንፃር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ለተማሪዎች፡- የማጠቃለል ብልሀትን በአንብቦ መረዳት እንዴት አድርገው ቢለማመዱና ቢጠቀሙአንድን ሰፊ ጽሑፍ ሀሳቡን ሳይለቅ በማሳጠር ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ችሎታ ከፍ ሊል እንደሚችል አቅጣጫን ይጠቁማል፡፡

ለቋንቋመምህራን፡-የተማሪዎቻቸውን የማጠቃለልብልሀትን በግልፅ በማስተማርና ባለማስተማር መካከል የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ የተሻለ አማራጭ የሚሆን አቅጣጫ በተግባር የተማሪዎችን ችሎታ ለማጎልበት ጥረት እንዲያደርጉ ጥቆማ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለተመራማሪዎች፡- በማጠቃለልየአንብቦ መረዳት ብልሀት አቀራረብ ዙሪያ እንዲሁም ማጠቃለል ይህን የአንብቦ መረዳት ብልሀት ከተለያዩ የተማሪዎች ባህሪያት አንፃር በሰፊው ለማጥናት ለሚሹ መነሻ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በማጠቃለል ብልሀት ማንበብን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና የሚመረምር ነው፡፡ ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሠኮሩ ወረዳ በደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም 10ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉትን የየምሳ አፍ ፊት ተማሪዎች የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ጥናት የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡ የደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያትም የአጥኚው የሥራ ቦታ በመሆኑ ለጥናቱ አመቺ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ሌሎች የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶችን አያካትትም፡፡10ኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በተገቢው መንገድ የተሻለ መረጃ መስጠት ይችላሉ ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የማጠቃለል ብልሀት ምንነት

ማጠቃለል ከቋንቋ ማስተማሪያ ብልሀቶች አንዱ ሆኖ አንድ በዝርዝር በሰፊው የቀረበን ጽሁፍ በማንበብ ሀሳቡን በታመቁና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ነው (Oxford 1990)፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመነሻ ጽሁፍንይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግንም ይፈልጋል፡፡

ማጠቃለል ለአንድ ጽሁፍ ጠቃሚ ሀሳቦችን ከመለየት ባሻገር ሀሳቦችን በተገጣጠመና በሰመረ መልኩ የመጻፍ ችሎታን የሚጠይቅ እንደሆነ Notom (1997) ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ Head and Andorson (1986)ን በመጥቀስ Doll and Others (1991) ማጠቃለልን ጸሀፊ-ተኮርና አንባቢ-ተኮር በሚል መክፈል የሚቻል መሆኑን ጠቁመው ተማሪዎች ጸሀፊ-ተኮር ማጠቃለልን እንዲለማመዱ በማድረግ ከመጻፍ ችሎታ ይልቅ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ እንደሚሻል አስገንዝበዋል፡፡

እንደ Doll and Others (1991) አገላለፅ ጸሀፊ-ተኮር ማጠቃለያ ዋናውን ጽሁፍ እያነበበ ማጠቃለያውን በሚጽፈው ሰው የሚነበብ በመሆኑ ለአደረጃጀትና ለጽህፈት ብዙም ትኩረት ሣይሰጥ ሊከወን የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የአንባቢው ትኩረት የጽሁፍን መልዕክት በመረዳት ላይ እንዲሆን እድል ይሰጣል፡፡

ይሁንና ብዙዎቹ ከማጠቃለል ብልሀት ጋር ተያይዘው ለተማሪዎቹ የሚሰጡ የአንብቦ መረዳት ተግባራት አንባቢ-ተኮር ማጠቃለያ ላይ እንዲያተኩሩ የሚያበረታቱ እንዲሆኑ Doll and Others (1991) ያመለክታሉ፡፡ ይህ የማጠቃለያ አቀራረብ ስልት ተማሪዎቹ ማጠቃለያውን ለሌላ አንባቢ በሚቀርብ መልኩ እንዲያዘጋጁ ስለሚጠበቅ ለጽሁፍ እርዝመት፣ ለሰዋሰው አወቃቀሩና ስለግጥምጥምነቱ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሀት የሆነውን ማጠቃለልን ከመረዳት ብልሀት ወደ መጻፍ ተግባርነቱ እንዲያመዝን የሚያደርጉት ይሆናሉ፡፡

ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ጠቃሚና ዝርዝር ሀሳቦችን ጨምቆ ማውጣትን እንደሚጠይቅ የሚያገናዝቡ Armbruister and Andobsom (2002) ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀትን ለማለማመድ በርካታ ቴክኒኮችን መጠቀም እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው ቴክኒክም የአንድን ቴክስት መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይነት ሀሳብን

የሚያመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን በማስፈር ተማሪዎቹ ጽሁፍን እያነበቡ በመሪ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር የሚካተቱ ሀሳቦችን እየለዩ እንዲያሰፍሩ በማድረግ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህም መምህሩ የሚያቀርባቸውን መሪ ሀሳቦች ተማሪዎቹ ጽሁፉን ሲያነቡ የትኛው ክፍል ላይ ማተኮር እንዳለባቸው የሚጠቁሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀትን ለመለማመድ የሚያስችል ትክኒክ እርከናዊ አጠቃሎ/Hierarchical summary/ Tayler and Bich (1984)፣ Taler and Berkiyutis (1980)፣በመጥቀስ Armbruister and Andobsom (2002) ያስረዳሉ፡፡ ይህን ቴክኒክም ለመተግበር በመነሻ ላይ ተማሪዎቹ ጽሁፍን እያነበቡ ርዕሶቹን፣ ንኡስ ርዕሶቹን እና አንቀፆቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ያዘጋጃሉ፡፡ በመቀጠልም በየርእሶቹ፣ በየንኡስ ርእሶቹና በየአንቀፆቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይተው ያወጣሉ፡፡ በመጨረሻም በየደረጃው ያወጧቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሳብን በማፍለቅና ዋና ዋና ሀሳቦችን በመሪው ሀሳብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡

የማጠቃለል ብልሀትን መሰረት በማድረግ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ሌላው አማራጭ ስልት በተለያዩ ተመራማሪዎች የተፈተሹና የዳበሩ የማጠቃለል አቀራረብ ህጎችን መጠቀም እንደሆነ Birawen and Diay (1983)ን እንዲሁም Riharit,Stahal, Arixen (1986)ን ዋቢ በማድረግ Armbruister and Andobsom (2002) ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህም ህጎች አላስፈላጊ መረጃዎችን ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ መሰረዝ፣ የተደጋገሙ መረጃዎች ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀም ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ የተገለጹ ሀይለቃሎች ወይም ዋና ሀሳቦች ካሉ እንደ መሪ ሀሳብ አድርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀጹን ዋና ሀሳብ በሀይለ ቃል መልኩ ያላሰፈረ ከሆነ የራስን ሀይለ ቃል መፍጠር ናቸው፡፡

## 2.1.1 በማጠቃለል ብልሀት ማንበብን ማስተማር የአንብቦ መረዳትን ክሂል ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ

ማጠቃለል ማለት ዋናውን ጽሁፍ በማሳጠር በጣም አስፈላጊ ነጥቦችን፣ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ አስፈላጊ ዝርዝሮችን ብቻ የያዘ ከዋናው ጽሁፍ ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነን ጽሁፍ ማደራጀት ነው፡፡ በማጠቃለል አላስፈላጊ መረጃዎችን በማስወጣትና አጠቃላይ ሀሳብን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር መሆኑን Denton and etal (2007)፣ ገልፀዋል፡፡ በDentonን አገላለጽ ስድስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡- ዋና ዋና ሀሳቦችን ማስፈር፣

አስፈላጊ ነጥቦችን ማስመር፣ የሚቻሉትን ማያያዝ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ማጠቃለያውን መጻፍና ማጠቃለያውን መከለስ/ማሻሻል ናቸው፡፡

አንድን በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍ በማንበብ ሀሳቡን በታመቀና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል ሲል Oxford (1990)፣ አብራርተዋል፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመነሻ ጽሁፉን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግን ይፈልጋል፡፡

አንድን ጽሁፍ ለማጠቃለል፣ የማጠቃለል ብልሀትን በመጠቀም ተማሪን ማለማመድ እንደሚቻል Armbruister and etal (2002)፣ ጠቁመዋል፡፡ ከስልቶች ውስጥ የጽሁፉን መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይ ሀሳቡን የሚያመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን ማስፈር በመሪ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር የሚካተቱ ሀሳቦችን መለየት፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀት እርከናዊ አጠቃሎ (Hierarchical summary) Tayler and Bich (1984)ን፣ Tayler and Berkoywites (1980)ን፣ በመጥቀስArmbruister and etal (2002)፣ አስረድተዋል፡፡ በዚህም ርዕሶቹን፣ ንዑስ ርዕሶቹን እና አንቀፆቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ማዘጋጀት፣ በመቀጠልም በየርዕሶቹ፣ በየንዑስ ርዕሶቹና በየአንቀፆቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይቶ ማውጣት፡፡ በመጨረሻም ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሳብን በማፍለቅ በመሪው ሀሣብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሳብ መጻፍ የሚሉ ናቸው፡፡ Birawon and Diay (1983)፣ Rahert (1986)ን ዋቢ በማድረግ Armbruister and etal (2002)፣ እንደጠቀሱት አላስፈላጊ መረጃዎችን፣ የተደጋገሙ መረጃዎች ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመተካት ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ የተገለፁ ሀይለ ቃሎች ወይም ዋና ሀሳቦች ካሉ እንደ መሪ ሀሳብ አድርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀፁን ዋና ሀሳብ በሀይለ ቃል መልኩ ያላሰፈረ ከሆነ በአንባቢው በኩል የራስን ሀይለ ቃል መፍጠር ናቸው፡፡

## 2.1.2በማጠቃለል ብልሀት አንብቦ መረዳትን በመማር ሂደት የተማሪዎች ባህሪያት ያላቸው ተፅዕኖ

የተማሪዎች ልዩ ልዩ ባህሪያት የመማር ብልሀቱን በሚመለከት የሚቀርበውን ትምህርት ስኬታማ ለማድረግም ሆነ በማደናቀፍ በኩል ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ የተማሪዎቹ የቋንቋ ብቃት ደረጃ፣ የመነቃቃት ሁኔታቸው፣ ፆታቸው፣ ቀደምት የትምህርት

ደረጃቸው፣ የመማር ስልቶች ምርጫዎቻቸው በብልሀቶች ስልጠና ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ Hilima (1998)፣ O'Malley & Chamot (1990)፣ Wondon (1992)፣ Wiliams & Burden (1997)፡፡

የቋንቋ ብቃት ደረጃቸውን በሚመለከት የብልሀት ትምህርቱ በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ የሚቀርብ ከሆነ በጀማሪ የትምህርት ደረጃ እያሉ ጀምሮ ሲቀርብላቸው በአግባቡ ሊከታተሉት ይችላሉ፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ ግን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶቹን ጨምሮ አብዛኞቹን ብልሀቶች ለማቅረብ የተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት የተሻለ ደረጃ ላይ እስከሚደርስ መጠበቅ አስፈላጊ ነው የሚል ሀሳብ ይሰነዘራልO'Malley & Chamot (1990)፡፡ ይሁን እንጂ Wondon (1987) ያደረጉትን ግለሰባዊ የሀሳብ ልውውጥ በመጥቀስ O'Malley & Chamot (1990) አያይዘው እንዳብራሩት ከሜታኮግኔቲቭ ስልቶች ጋር የተያያዙ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለተማሪዎቹ ቀድመው በማስተዋወቅ ትምህርቱን መስጠት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አንዳንዶቹን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙት በቋንቋው የዳበረ እውቀት ለሌላቸው ተማሪዎች ማቅረብ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚጠቁሙ ጽሁፍት አሉ፤ ለአብነትም Berih and Berchanden (1984)፣ Tayler and Bich (1984)ን በመጥቀስ Dolle and Others(1991) እንደጠቆሙት የማጠቃለል ብልሀት መካከለኛና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች መቅረብ ያለበት ነው፡፡ ከስድስተኛ ክፍል በታች ያሉ ብዙዎቹ ተማሪዎች ቁልፍ የሆኑና ያልሆኑ ሀሳቦችን አንብበው በመለየት በኩል ችግር ስለሚያጋጥማቸው የማስታወሻ አያያዝ ብልሀትን ማስተማር አስቸጋሪ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ ብልሀቶችን በማስተማር ሂደት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ሌላው ነጥብ የተማሪዎች ፍላጎት ሁኔታ ነው፡፡ ብልሀቶቹን በማስተማር ሂደቱ በመነሻ ላይ ተማሪዎች ጥሩ የመነቃቃት ሁኔታ ላይታይባቸው የችላልWondon (1992)፡፡ Paris (1988)ን ዋቢ በማድረግ O'Malley & Chamot (1990) እንዳሰፈሩት በብልሀቶች ትምህርት ውስጥ ምሪትን፣ ቀጥተኛ ገለፃን፣ በድጋሚ ማስተማርንና ተማሪዎቹ በጋራ የሚማሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት መነቃቃትን መፍጠር ይጠበቃል፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪዎቹ ከዕለት ወደ ዕለት የሚያመጡትን የመነቃቃትና የግንዛቤ ለውጥ መፈተሽ ተገቢ ይሆናል፡፡ ያመጡትን ለውጥም ለመፈተሽ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የማመሳከሪያ ቅፅን በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ Wondon (1992)፣ Brown (1994)፣ Wiliams and Burden (1997) አስገንዝበዋል፡፡ ብልሀቶችን በመማር ሂደት ሊተኮርበት የሚገባው

ሌላው የተማሪዎች ባህሪ የመማር ስልት ምርጫዎቻቸው ልዩነት ነው፡፡ Willing (1989) በማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የመማር ስልቶች ምርጫ ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ የተለያዩ የመማር ስልቶች ምርጫዎች ያላቸውን ተማሪዎች ለተለያዩ የመማር ብልሀቶች አቀራረብ የሚሰጡት ምላሽም ተመሳሳይ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ያህል ጀማሪ ለሆኑ፣ ከፍተኛ አውድ ጥገኝነት ለሚታይባቸው በተናጠል መስራት ለሚመርጡና ነገሮችን ለመተንተን ምርጫ ያላቸው ብልሀቶችን እየዘረዘሩ በቀጥታ ማቅረብን ወይም መማርን አይመርጡም፡፡ ለተማሪዎች የመማር ስልቶችና የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ትምህርት አቀራረብ ምርጫዎቻቸው መካከልም ዝምድና እንዳለ በጥናቶች ለመፈተሽ ሙከራ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ተማሪዎችን እንደ መማር ስልቶች ምርጫዎቻቸው ማስተማር ከውጤታቸው መሻሻል ጋር ግንኙነት እንደሌለው የሚያመለክቱ ጥናቶች አሉ፡፡ ለምሳሌም Muler (1992), ዋቢ ያደረጋቸው Kronbah and Vonow (1977)፣ Campwreze and Batas (1980)፣ Temadan (1999) ባደረጓቸው ጥናቶች ተማሪዎችን እንደመማር ስልት ምርጫዎቻቸው ማስተማር ውጤታቸውን ያሻሽላል የሚለውን አስተሳሰብ የሚቃረን ውጤት ማሳየታቸው ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም Clark (1982) በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች በሚመርጡት የማስተማር ዘዴና በውጤታቸው መካከል ተዛምዶ እንደሌለ Muller (1992) አመላክተዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የተገለፀው አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ከሚመርጡት የመማር ስልት የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም ሊማሩ መቻላቸው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በቀጥታ መማር ከተማሪዎች የተለያዩ የመማር ስልቶች ምርጫዎች ዝምድና ያለው ወይም የሌለው መሆኑን በጥናት ቢፈተሽ የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

## 2.1.3 የማንበብና አንብቦ የመረዳትምንነት

### 2.1.3.1 የማንበብምንነት

እንደ ግንቢቱ ዲበኩሉ (2010)፣ ፍቅሬጠና ጋሻው (2012) እና አደይ ብርሃኑ (2011) አገላለፅ ማንበብ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ለተማሪዎች ከሚያስፈልጓቸውና እጅግ ከሚጠቅሟቸው ክሂሎች አንዱ ነው (Campbell, Kelly, Mullis, Martin and Sainsbury 2001)፡፡ Campbell,et al (2001) እንደሚያብራሩት የማንበብ ክሂል ለፈጠራና ለግላዊ እድገት ጠቀሜታ ስላለው በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ከማንኛውም ክሂል በበለጠ ትኩረት የሚፈልግ ነው፡፡ እንዲሁም

ታዳጊ ህፃናት በማህበረሰባቸው ውስጥ ወይም በሰፊ ህብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ዝግጁነታቸውም ይጨምራል፡፡ በሌላ አገላለጽ በቅድመ ትምህርት ጊዜ ወላጆች በቤት ውስጥ ሊያዳብሩት የሚገባ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልግ ክሂል ነው፡፡

ውስብስብ የሆነው የማንበብ ሂደት በተለያዩ የትምህርት መስኮች በርካታ ምርምር ተሰርቶበታል፤ እየተሰራበትም ይገኛል (Janan, 2011)፡፡ ነገር ግን በብያኔው፣ በሂደቱ፣ በአቀራረቡና በዘዴው ውጤታማነት ዙሪያ አሁንም ድረስ አንድ ወጥ ድምዳሜ ላይ አልተደረሰም፡፡ ብያኔውና በየጊዜው የነበረውን የትኩረት መውጣትና መውረድ፣ መስፋትና መጥበብ Stahal (1998) ሲገልጹት በማንበብ ውስጥ አጠቃልይ ከሆነው የቃላት ሰነ ዘዴ ወደ ድምጽ መለየት ከዚያም አጠቃላይ ወደ ሆነው የቋንቋው መመሪያ ተሸጋግረናል፡፡ ሽግግሩም የምርምሩን አቅጣጫ እንዲቀያየር አድርጎታል ይላሉ፡፡

የምርምሩ ትኩረት መለያየት ደግሞ ማንበብን የተለያየ ብያኔና ባህርይ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ከባህርያቶቹ መካከል የታተሙ ጽሁፎችን መረዳት፣ ቋንቋውን መገንዘብና በታተሙ ገጾች አማካኝነት አዕምሮን የማሳደግ ጥበብ ይጠቀሳሉ (Walcutt, 1967)፡፡ Walcutt, (1987) እንደሚያብራሩት ማንበብን ለመበየን ሁለት ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ እነሱም በጊዜው የንሰራራው ንድፈ ሀሳብና ተግባር ናቸው፡፡ Campbell,et al (2001) የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሲተረጉሙት አንብቦ መረዳት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብን የያዘ ሲሆን ፊደላትን አገጣጥሞ ቃላት መስርቶ ቃላትን ገጣጥሞ አረፍተ ነገር መስርቶ መልዕክት የመውሰድና መልዕክቱን የማንፀባረቅ ሂደት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የተጻፉ ጽሁፎችን የመረዳት ችሎታና የተረዳውን ነገር ማህበረሰቡ ወይም ግለሰቡ በሚፈልገው መንገድ መጠቀም ማለት ነው፡፡

እንደየ ዘመኑ የትምህርት ትኩረትና የሚገኙ የትምህርት መሳሪያዎች ልዩነት ለማንበብ የተለያየ ብያኔና ባህርይ እንዳሉት ቢገለጽም ከሁሉም እይታዎች የሚገኘው የጋራ ብያኔ ከሚታዩ ምልክቶች ወይም በምልክት አማካኝነት ከተፃፉ ጽሁፎች መልዕክት መቀበያ መንገድ መሆኑን ነው፡፡ በጥንትም ሆነ በአሁኑ ዘመን በማንበብ ላይ ያተኮሩ ተመራማሪዎች ሁሉ በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን የቅርብ ጊዜ አጥኚዎች ዘመኑ ከፈጠራቸው የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ጋር ለማጣጣም ከሚታዩ ምልክቶች ወይም ከሚጻፉ ጽሁፎች በተጨማሪ ከኤሌክትሮኒክስ መስኮቶችም መረጃዎችን የማግኘት ሂደት እንደሆነ Janan (2011) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.3.2 የአንብቦመረዳትችሎታምንነት

እንደ ባንቿአምላክ ፈጠነ (2013)፣ ሠርካለም ይገረሙ (2010) እና ማስተዋል ውበቱ (1989) አገላለፅ ሰዎች ለንባብ እና አንብቦ መረዳት ችሎታ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ይሰጣሉ፡፡Campbell,et al(2001) እንዳብራሩት ማንበብ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ለተማሪዎች ከሚያስፈልጓቸውና እጅግ ከሚጠቅሟቸው ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ለፈጠራና ለግላዊእድገት ጠቀሜታ ስላለው በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ከማንኛውም ክሂል በበለጠ ትኩረት የሚፈልግ ነው፡፡ እንዲሁም ታዳጊ ህፃናት በማህበረሰባቸው ውስጥ ወይም በሰፊ ህብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፣ ዝግጁነታቸውንም ይጨምራል፡፡ በሌላ አገላለጽ በቅድመ ትምህርት ጊዜ ወላጆች በቤት ውስጥ ሊያዳብሩት የሚገባ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልግ ክሂል ነው፡፡

የአንብቦ መረዳትን ክሂል ምንነት በተመለከተ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ በማውጣት ጽሁፍን የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡ አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈለገውን መረጃ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤን የሚመለከት ነው (Williams, 1990)፡፡ Grellet (1981) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት ማለት ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ አንባቢው ወይም ተማሪው እስከሚቻለው ድረስ በብቃት የሚፈለገውን መረጃ ማውጣት መቻል ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ እመቤት (2011) አንድ ተማሪ ወይም አንባቢ የሚያነብበትን ዓላማ አውቆ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችለውን መረጃ ካገኘና ለይቶ ካወጣ አንብቦ ተረድቷል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት ማለት የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ለይቶ ማውጣት ሲሆን አጠቃላይ የጽሁፍን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡

Carrell and Grabe (2010) አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ መረጃ ማግኘትን፣ መገንዘብን፣ እውቀት ከችግር ጋር ማዛመድን የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ Thonis (1970) ደግሞ ንባብ ለሌሎች ችሎታዎች የሚፈለግ ተግባር ነው ይላሉ፡፡ Broughton,et al (2003) ንባብ ውስብስብ ችሎታ ነው፡፡ እንደ Nunan (1991) ገለፃ ንባብ የሚነበበው ነገር ከአንባቢው ጋር መስተጋብር የሚፈጥሩበት ብቸኛ መንገድ ነው፡፡ Vaugh (2012) አንብቦ መረዳት አንባቢው ከደራሲያን ዳራዊ እውቀት ጋር የቀረበውን መረጃ በማጣመር ትርጉም የመገንባት ሂደት ነው፡፡ አንባቢው

ትርጉሙን ለመገንባት ከጽሁፉ ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ውስብስብ የግንዛቤ ችሎታዎችን እና ስልቶችን ያከናውናል፡፡

ከመረዳት ሂደት በስተ ጀርባ በጽሁፍ፣ በአንባቢውና በደራሲው መካከል፣ ዕውቀትን መጨመር፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ግልጽ ማድረግ እና ግንዛቤን መጨበጥን በመሳሰሉ ተከታታይ የሀሳብ ልውውጥን ያጠቃልላል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ Grellet (1991) አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አውድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት መሰብሰብ መቻል ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈለግ መረጃን በመተው የሚፈለገውን ዓይነት ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡Smith (1985) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት አንባቢው ቀድሞ ይዟቸው ለተነሳው ጥያቄዎች መልስ የሚያገኝበት ክሂል ነው፡፡ ጥያቄ መጠየቅ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ባህርይ ነው፡፡ አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ካገኘ በአንባቢውና በጸሀፊው መካከል ተግባቦት ይፈጠራል፡፡ ተግባቦት የሚኖረው ደግሞ መረዳት ሲኖር ነው፡፡

ሙሉገበያ ያለው (2009) ሰለሞን (2003)ን ጠቅሶ አንብቦ የመረዳት ክሂል የሚከተሉትን ነጥቦች እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡

ሀ.የቃላትን በፍቺ መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍች ሊረዳ ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ ስላልሆነ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም፡፡

ለ.የጽሁፉን ግልጽ መልዕክት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክትና ይህንን መልዕክት ለማጎልበት ሆነ ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሀሳቦች መረዳት የሚመለከት ነው፡፡

ሐ.የጽሁፉን ውስጣዊ መልዕክት መረዳት፣ በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልዕክት መገንዘብ የአንብቦ መረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚህ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም፡፡ በግልጽ የተመለከተውን መልዕክት መነሻ በማድረግ በመገንዘብና በመመርመር የሚደርስበትን ውስጣዊ መልዕክት መረዳት ይጠበቅበታል፡፡

መ. የአያያዦችን ሰዋሰዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን አገባብ፣ አገልግሎትና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህን መገንዘቡ የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክትለታል፡፡ የጽሁፉን ቅደም ተከተልና የሀሳብ ፍሰት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን

ዐረፍተ ነገሮች ተናጠላዊ መልዕክት መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ አንዱ ዐረፍተ ነገር ከፊተኛው ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነት የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስ በርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል፤ የሚሉት ነጥቦች የአንብቦ መረዳት አካላት ናቸው፡፡

Shanchan (2006) አንብቦ መረዳት የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መረዳትንና በሚገባ መጨበጥን የሚገልጽ እሳቤ እንደሆነና የጸሀፊውን ሀሳብ ወይም መልዕክት መለየትን፣ አውዳዊ ፍችዎችን መገንዘብና ከአውዱ ውጭ የሆኑ ፍችዎችንም መረዳትን የሚያጠቃልል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ አንብቦ መረዳትን በሁለት ይከፍሉታል፡፡ አንደኛው በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በምንባቡ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ የሚረዱበትን ሁኔታ ይጠቁማል፡፡

Madson (1983) እንደ ገለጹት የአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ ፈተና ነው፡፡ Nuttal (1996) and Madson (1983) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በማዛመድ፣ ትንበያ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በአጭር መልስ ስጥ፣ በምርጫ እና ክፍት ቦታ ሙላ በማለት መጠየቅ እንደ ሚቻል ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳብ የምንረዳው አንብቦ መረዳት አንባቢ የጸሀፊውን ሀሳብና አመለካከት ለመረዳት ሲል ከጽሁፍ ያገኘውን ሀሳብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር እያገናዘበ የራሱ አዲስ አመለካከት የሚንጸባረቅበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የአንብቦ መረዳት ፈተና ዋና መሳሪያ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.1.3.3 የአንብቦመረዳትሞዴሎች

በ1960 ዎቹና 1970 ዎቹ የነበረው የአንብቦ መረዳት ሞዴል አንብቦ መረዳትን ከመጻህፍት፣ ከታሪኮችና ጆርናሎች መረጃ የመሰብሰብና የማቀናጀት ሂደት በሚል ይገልጹታል (Fox and Alexander,2009)፡፡ በዚህ ዘመን ከአንባቢው የሚጠበቀው ግብአት ከጽሁፍ ውስጥ ተገቢውን መልዕክት ማውጣት ስለነበር በጊዜው ተስፋፍቶ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ሞዴል የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል (Extraction-Assembly Model) ነበር (Fox and Alexander,2009)፡፡

በ1980ዎቹ አካባቢ አንብቦ መረዳት እይታው ባለሁለት አቅጣጫ እንደሆነ Fox and Alexander (2009) ያስረዳሉ፡፡ ማለትም ጽሁፉን ለመረዳት የአንባቢው ቅድመ እውቀትና አውድ ወሳኝ ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የነበረው የማንበብ ሂደት ሞዴል የመገንባትና የማዋሀድ ሞዴል (Constructive-Integrative Model) በጽሁፉ መልዕክት ላይ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ግለሰባዊ መልስ እንዲሰጥ በመፍቀዱ ጽሁፉ ከአንድ በላይ ትርጉም ይኖረዋል (Fox and Alexander,2009)፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የአንብቦ መረዳት ክሂል ትኩረት በተለያዩ ባህላዊና አማራጫዊ አውዶች ላይ ማጠንጠን ጀመረ (Fox and Alexander,2009)፡፡ ምክንያቱም ከለውጡ መረዳት እንደ ሚቻለው ጽሁፍ በማህበረ ባህላዊ አውድና ማህበራዊ ትስስር መዳበሩንና አንብቦ መረዳት ውጤታማ የሚሆነው በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ ማጠንጠን ሲችል ነው፡፡ እንደ Fox and Alexander (2009) ቅኝት አንብቦ መረዳት በመረጃ መረብ የሚገኙ መጽሐፎችን መጠቀም፣ ኮምፒውተር በመጠቀም ዋቢዎችን ማጣቀስ፣ ዋቢዎችን በተገቢው ማደራጀት፣ በመረጃ መረብ የሚገኙ ጋዜጦችን ቅርጽና ዘውግ መለየት፣ የኮምፒውተር ጽሁፎችን ከታተሙ ጽሁፎች ጋር ማወዳደር፣ የተጠቀሱ ምንጮችና በየመካከሉ የገቡ ስዕሎችና ግራፎችን ሚና መለየት፣ በኮምፒውተር የቀረቡ ጽሁፎችን ከድምጽና ምስል ጋር ማቀናጀትን ሁሉ ያካትታል፡፡ የእነዚህ ነገሮች መካተት አዲሱን የተሻጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል እንዲታወቅ አድርጓል (Fox and Alexander,2009)፡፡

በአጠቃላይ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስካለንበት ጊዜ ድረስ በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰሩ ምርምሮች የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል፣ የመገንባትና የማዋሀድ ሞዴል እና ተሸጋጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል የሚባሉ ሦስት የተለያዩ ሞዴሎችን አስገኝቷል፡፡ የሞዴሎቹ መለያየትም በማንበብ ሂደት ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ስለአንብቦ መረዳት ሌላው መነሳት ያለበት ነጥብ እንዴት ይለካል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ Leslie and Caldwell (2009) እንደ አስገነዘቡት አንብቦ መረዳትን መለኪያ ዘዴዎች መደበኛና ኢ-መደበኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ቀደምት የመደበኛ መለኪያ ዘዴዎች አጭር አንቀጽ መጠቀምና ምርጫን ያካትታሉ፡፡ ምርጫ በመጠቀም የሚለኩ ክሂሎችን በዘጠኝ ቡድኖች እንደሚከተለው ከፍለዋቸዋል፡፡

1)የቃላትን ትርጉም ማስታወስ 2)ከይዘቱ ውስጥ ያሉትን ቃላት ትርጉም ማጠቃለል 3)የምንባቡን ቅርጽ መከተል 4)የምንባቡን ዋና ሀሳብ ማቀናጀት 5)በምንባቡ በግልጽ

ወይም በስውር የቀረቡ ይዘቶችን መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት 6) ሀሳቦችን በተለያየ አቅጣጫ መረዳት 7) ከይዘቱ ማጠቃለያ ማውጣት 8)የጸሀፊውን ቴክኒክ መለየትና 9)የጸሀፊውን አላማ ፣ድምጸትና አካሄድ መለየት ናቸው፡፡

ከ1970 ዎቹ እስከ 1980 ዎቹ መጀመሪያ ባሉት ጊዜያት የአንብቦ መረዳት መለኪያ የሚያጠነጥነው ቅደምተከተል በመጠበቅ፣ ዋናውን ሀሳብ በማግኘትና በማጠቃለል ክሂሎች ላይ ሲሆን በ1980 ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ረጅም ምንባቦችን እንዲሁም ቀደምት እውቀትና ብልሀትንም በመጨመር መለካት ተጀመረ (Leslie and Caldwell,2009)፡፡ ነገር ግን በ2000 መግቢያ ላይ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የምንባቡ፣ የጥያቄዎቹ፣ የሰዎቹ፣ የምንባቡ ዘውግና ጭብጥ የመሳሰሉ ተላውጦዎች ተፅዕኖ አብሮ መታየት እንደ ተጀመረ Leslie and Caldwell(2009) የስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ የአንብቦ መረዳት መደበኛ መለኪያ መሳሪያ ጥያቄዎችን፣ ማስታወስ ወይም እንደገና ማለት፣ ኢ-መደበኛ የማንበብ አጋጣሚዎች፣ ግልጽ ውይይቶች፣ አረፍተ ነገር የመለየት ተግባራትና የተለያዩ የመለኪያ ዘዴዎችን በዋናው ስር ማደራጀት የመሳሰሉ ኢ-መደበኛ መለኪያ መሳሪያዎችን ያካትታሉ (Leslie and Caldwell,2009)፡፡

## 2.1.3.4 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ

የዚህ ጥናት ትኩረት የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን ከመፃፍ ክሂል ጋር አገናኝቶ በማቅረብ ሊኖር የሚችለውን አስተዋፆ መመርመር በመሆኑ አቀራረቦቹን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

የንባብ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ክንዋኔዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006) ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎች ለምንባቡ የሚኖራቸውን እውቀት ከወዲሁ ለመጠቀም የሚያገለግለን ነው፡፡

**የቅድመ ንባብ ተግባራት አስፈላጊነትም ፡-**

- ተማሪዎችን ለንባብ ለማዘጋጀት
- ተማሪዎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ እውቀት ለማረጋገጥ
- የንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ እና ሌሎችም ጠቀሜታዎች አላቸው፡፡

ቅድመ ንባብ ተግባራት በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡ እነሱም ፡-

1.በጥያቄና መልስ መልኩ ይካሄዳል፡፡

2.ድርጊቶችን በማከናወን / ለምሳሌ፡- ስዕሎች መሳል እና ችግር ፈች በሆኑ ጥያቄዎች ዙሪያእንዲወያዩ በማድረግ ይካሄዳል በማለት Lindsay and Knight (2006) ገልፀዋል፡፡

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሚነበበውን ጽሁፍ አስመልክቶ ከንባብ በፊት የሚሰሩ በመሆናቸው የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ እነሱም፡-

- ተማሪዎቹ ቀድመው ስለሚዘጋጁ ወደ ዋናው ምንባብ በሚገቡበት ጊዜ ምን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ያውቃሉ፡፡ ይህም መማርን ቀላል፣ ተፈጥሯዊና ትርጉማዊ ያደርገዋል፡፡
- ቅድመ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛሉ፣ ልምዳቸውን፣ ሀሳባቸውንና ጽሁፉን አስመልክቶ የገመቱትን ከማንበባቸው በፊት ስለሚለዋወጡ የተሻለ ግንዛቤ ይዘው ያነባሉ፡፡
- ቅድመ ንባብ የመማር ክሂልን መማሪያም ነው፤ተግባራቱ ተማሪዎቹ ጽሁፍን እንዴት እንደሚያነቡ ወይም እንዴት እንደሚያቀርቡት የሚያመለክቱ በመሆናቸው ለራሳቸው የንባብ ስራ ሀላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያጎለብትላቸዋል፡፡
- ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጽሁፍ አስቀድመው በጋራ እንዲሰሩና የጋራ ግንዛቤያቸውን ይዘው እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡
- የመገመት ተግባራቱ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ሲሆኑ ከሚነበበው ጽሁፍ ምን እንደሚጠበቅ በማመላከት ጽሁፉን የማንበብ ፍላጎትን ይጨምራል፡፡
- ተማሪዎች ቀድመው የገመቱትን ወይም የሚጠብቁትን ከሚያነቡት ጋር እያነፃፀሩ እንዲያነቡ ያግዛል፡፡
- ሰዎች አዲስና ያልታወቀ ነገር ይፈትናቸዋል፡፡ ለዚህም ቅድመ ንባብ ተግባራት በሚነበብ ጽሁፍ ውስጥ እንግዳ ነገር ወይም ችግር ሲያጋጥም እንዴት መፍታት እንደሚቻል መንገድ ያመላክታል፡፡
- ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን ቋንቋውን በጥልቀት የመማር ፍላጎት ይጨምራሉ፡፡ ነገሮችን በጥልቀትና በስፋት የማየትና የመረዳት ችሎታን ያሳድጋሉ፡፡

**የንባብ ጊዜ ተግባራት፡-** በዚህ የንባብ ጊዜ ተግባር ወቅት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት ላይ የተመሰረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበትና ተማሪዎቹ የበለጠ ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያግዙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የንባብ ጊዜ እያነበቡ ያሉ ተማሪዎችን በርካታ ተግባራትን ማሰራት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተግባራት እንደ ምንባቡ ይዘትና አላማ ይለያያሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ Lindsay and knight (2006)የንባብ ጊዜ ተግባራትን በሦስት መንገድ ገልፀዋል፡፡

እነሱም፡-

- የተማሪና የመምህር ጥምረት ተግባራት
- የተማሪ ከተማሪ ጥምረት ተግባራት
- የጽሁፍ ተግባራት ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

**ድህረ ንባብ ተግባራት፡-** ድህረ ንባብ ከንባብ ሂደት በኋላ የሚሰጡ ጥያቄዎች የሚሰሩበት ሂደት ነው፡፡ እንዲሁም በንባብ ማጠናቀቂያ ጊዜ የሚታዩ ሲሆን የንባብ ሂደት የሚከለስበት ነው፡፡ ድህረ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን ሙሉ በሙሉ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፤ የምንባቡን ተአማኒነት እንዲገመግሙ ለማበረታታት እና ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙ ለማድረግ የሚጠቅም ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ ከተነሱባቸው የቅድመ ንባብና በመቀጠልም በንባብ ጊዜ ከተሳተፉባቸው ጥያቄዎች በተረዱቸው ሀሳቦች መሰረት የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች የሚያካትት ተግባራዊ ክንውንን ይይዛል፡፡ በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ሲሆን ምንባቡን መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማዛመድ ሀሳብ እንደ ሚያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ከራሳቸው የህይወት ልምድና እውቀት አኳያ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ተጠቅመው ሀሳብ የሚሰነዝሩበት ነው፡፡ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች ለአሳታፊነታቸው እንጂ ለውጤት ተብለው መዘጋጀት የለባቸውም፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለዚህ ጥናት የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን ከመጻፍ ክሂል ጋር በማገናኘት ለማቅረብ ይሞከራል፡፡ ይህም የሚከናወነው በያንዳንዱ ክንዋኔ የሚካተቱ ጥያቄዎች ከመፃፍ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ ይሆናል፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ስለማንበብ ክሂል የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በሀገር ውስጥ የተሰሩ ጥናቶች በአብዛኛው በአንብቦ መረዳት ላይና ለአንብቦ መረዳት የሚውሉ ግብዓቶች ማለትም

የፅሁፍ ቅንጫቢዎችና ልቦለዶችን በመጠቀም እንዲሁም ለአንብቦ መረዳት ትብብራዊ መማር ዘዴ ያላቸውን አስተዋጽኦ የሚያሳዩ ጉዳዮችን አጥኚው ባደረገው ዳሰሳ ለማየት ችሏል፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹን ለማየት ይሞክራል፡፡

የመጀመሪያው የገብረመድህን ተስፋው (2011) ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን "የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ሚና፣ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ያካሄደው ነው፡፡

የጥናቱ ዓላማምየማጠቃለል ብልሀትን ተጠቅሞየተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡በተጨማሪምበወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ልዩነት ስለመኖሩ መፈተሽ ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካት ምርምሩ በመጠናዊ እና በአይነታዊ ዘዴ መረጃዎችን በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ አይነቶች አማካኝነት በመሰብሰብ የመተንተንና የመተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የተደረሰበት ድምዳሜ በማጠቃለል ብልሀት የተማሩ የአማርኛአፍ ፈት ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታየተሻለ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናት ከገብረመድህን (2011) ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በማጠቃለል ብልሀት በማስተማር የማንበብ ክሂል ችሎታን መፈተሽ ሲሆን፤ጥናቶቹን የተለያዩ የሚያደርጋቸው የገብረመድህን ጥናት በአማርኛ አፍ-ፈት በሆኑ ተማሪዎች እና ፆታ ተኮር ጥናት ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ በኢ- አፍ ፈት ላይ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላውየታምሩ (2008) ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እናስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን "በበርትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ጾታ ተኮር ጥናት" በሚል ርዕስ ያካሄደው ነው፡፡

የጥናቱ ዓላማም በበርትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት መመርመርና በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ለመሆኑ ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መፈተሽ ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካት ምርምሩ በመጠናዊ ዘዴ መረጃዎችን በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ አይነቶች አማካኝነት በመሰብሰብ የመተንተንና የመተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የተደረሰበት ድምዳሜ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በበርትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ በቂ መሆኑንና በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከልአንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናት ከታምሩ (2008) ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በተመሳሳይ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ችሎታን መፈተሽ ሲሆን ጥናቶችን የተለያዩ የሚያደርጋቸው የታምሩ ጥናት የተማሪዎቹ የክፍል ደረጃና በአማርኛ አፈ-ፈት እና ኢ አፍ ፈት በሆኑ ተማሪዎች እንድሁም የታምሩ ጥናት ያታ ተኮርሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው ደግሞ የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የታምሩ የመረጃ መሰብሰቢያ በመጠናዊ ዘዴ ሲሆን ይህ ጥናት የሚጠቀመው ግን በመጠናዊና አይነታዊ (ቅይጥ) ዘዴ በመሆኑ ይለያል፡፡

እንዲሁም የከድር (2008)ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን "በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሀ ትምህርት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ" በሚል ርዕስ በያዩ አይዳቲያ እና የሞቦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ዓላማዎች ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሀ ትምህርቱ ላይ ከተቀመጠው ዓጥጋቢ መማር ማስተማር ብቃት ማረጋገጫ (MLC) ላይ መድረስ አለመድረሱን መፈተሽ ሲሆን መረጃዎች የሰበሰበባቸው በመጠናዊና አይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለተማሪዎች የንባብ ችሎታ መለኪያ ፈተና እና ለመምህራን በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያመለክተውም በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች በተሰጣቸው አንብቦ መረዳት ፈተናዎች በጣም ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጠው የችሎታ ብቃት ማረጋገጫ (MLC) ላይ እንዳልደረሰ አመልክቷል፡፡

ይህ ጥናት ከከድር (2008) ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች የአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህን ጥናቶች የተለያየ የሚያደርጋቸው የከድር ጥናት አንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሀ ትምህርት ጋር ያለው

ተጣጥሞሽ ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ የሚፈትሽ በመሆኑ ነው፡፡

በመጨረሻም የመሪነሽ (2004) ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂይማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ነው፡፡ "የማንበብ ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ" በሚል ርዕስ በጎንደር ከተማ የእድገት ፈለግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጎ የተሰራ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በማንበብ ተነሳሽነት እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችባቸው መሳሪያዎች ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያመለክተውም በፆታና በማንበብ ተነሳሽነት መካከል፣ በፆታዊና በውስጣዊ የንባብ ተነሳሽነት መካከል፣ በፆታና በአንብቦ መረዳት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩንነው፡፡ ነገር ግን በፆታና በውጫዊ የማንበብ ተነሳሽነት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን በዚህም ሴት ተማሪዎች በአንፃሩ ከወንድ ተማሪዎች ጉልህ ብልጫ ያላቸው መሆኑን በጥናቷ አመላክታለች፡፡

ይህ ጥናት ከመሪነሽ (2004) ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች የአማርኛ ቋንቋ በማንበብ ክሂል ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ነው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ የመሪነሽ ጥናት የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ መፈተሽ መሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው አጥኚው በዳሰሳ እንደተመለከተው በሀገር ውስጥ የተጠኑት ጥናቶች ለአንብቦ መረዳት የተለያዩ ግብዓቶች ያላቸውን ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው የዚህ ጥናት አጥኚ ያምናል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ይህንን ብልሀት የዳሰሱበት ሁኔታ ስለሌለ ክፍተት ነው ብሎ በማመን ይህንን ክፍተት ለማየት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ከሆኑት መካከል የማጠቃለል ብልሀትን ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ ለመዳሰስ ተነሳስቷል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ ሲሆን የሚከተለው የጥናት ዓይነት ቅይጥ የአጠናን ዓይነት ነው፡፡ የሁለት ቡድኖች ማለትም የቁጥጥር ቡድን እናየሙከራ ቡድኖች የቅድመና ድህረ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ሁለቱ ተጠኝ ቡድኖች ምንም ሳይማሩና ከተማሩ በኋላ ባስመዘገቧቸው የፈተና ውጤቶች አማካይነትያሳዩትን የማንበብ ክሂል ልዩነት ምርምሯል፡፡ ይህንንም ለማካሄድ የሚከተለውን ሂደት ተከትሏል፡፡

የጥናቱ ሂደት ተገቢ የሆነውን መንገድ እንዲከተል በመጀመሪያ ለጥናት የተመረጠው ትምህርት ቤት በመገኘት በታላሚ ናሙና የሚለዩትን ክፍሎች መምህራን ፈቃድ ተወስዷል፡፡ በቀጣይ ለዚህ ጥናት የተመረጡትን ተማሪዎች በአካል በመገኘት በቀጣይ የመማር ማስተማር ሂደት በመማር ማስተማሩ ክፍለ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር እንደመጣ በመግለፅና ዓላማውን በግልፅ በማስረዳት ወደተግባር ተገብቷል፡፡ በቀጣይም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ የሆነውን ፈተና ጥያቄ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ጥያቄ የቅድመ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ ከዚያም የተዘጋጁት ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥ የዚህ ጥናት አማካሪን የተዘጋጁትን ምንባቦችና ጥያቄዎች በማስገምገምና በተጨማሪም በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ከአጋር መምህራን ተጨማሪ ግብዓት በመውሰድ ማሻሻያ በማድረግ ለፈተና ቀርበዋል፡፡

በዚህ ጊዜ የሙከራና የቁጥጥር ክፍሎች ተመሳሳይ በሆነ ጊዜና የጊዜ ርዝማኔ በተመሳሳይ ጊዜ ተሰጥተዋል፡፡ ከዚያም የፈተና ወረቀቶቹ ተሰብስበው በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ታርሞ የሦስቱን መምህራን አማካይ ውጤት በመውሰድ በውጤት ትንተናው አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂል የሚኖራቸውን ችሎታ ለመለየት ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን የመጀመሪያ ደረጃ ከሆነው የቅድመ ትምህርት ፈተና መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በተመደበላቸው የመማር ማስተማር ሂደት በተቃራኒ ፈረቃ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ለማስተማር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች “ባጎረስኩት እጄን ተነከስኩ”፣ “የሴቷ

መንገድ"፤ "የጉሌለው ሰካራም"፤ "የሥራ ያገኛል"የሚሉትን ርዕሶችለማስተማሪያነት ተዘጋጅተዋል፡፡

በሙከራው ጥናት የትግበራ ወቅት ተማሪዎች ሁለቱንም ቡድኖች ከሚያዚያ 1/2015 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ለአራት ሳምንታት አንብቦ የመረዳት ትምህርት ለሙከራ ቡድን የማጠቃለል ብልሀትን ብቻ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደት በመከተል ተምረዋል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በሰኮሩ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የደነባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይኸውም አጥኚው በዚህ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እያገለገለ ስለሆነ ጥናቱን ለማካሄድም ሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ጥናቱን ለመስራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርልኛል ብሎ በማሰቡ ነው፡፡

### 3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው ትምህርት ቤት ውስጥ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ፡፡ አራቱ መምህራን በመረጃ ሰጪነት በጠቅላይ ንሞናዘዴተመርጠዋል፡፡

### 3.2.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በጥናቱ ተተኳሪው ትምህርት ቤት ከ9ኛ እስከ 12ኛ የክፍል ደረጃዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ10ኛ ክፍል በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይህም ክፍል የተመረጠበት ምክንያት የተሻለ መረጃን መስጠት ይችላሉ ተብሎ በአጥኚው በመታሰቡ ነው፡፡

### 3.2.4 የምድብ (ሴክሽን) እና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በናሙናነት የተመረጡት አራት መምህራን የ10ኛ ክፍል ምድቦችን (ሴክሽን) ያስተምራሉ፡፡ ስለሆነም ከሚገቡባቸው ምድቦች ውስጥ ሁለቱን ምድቦች (ሴክሽን) በቀላል የዕጣንሞና ዘዴ አማካኝነት (10ኛB፣ 10ኛD) ሁለት ምድቦች ተመርጠዋል፡፡ከተመረጡት ሁለት የ10ኛ ክፍል ውስጥ ከየምድባቸው በአላማ ተኮር ዘዴ በየምሳ አፋቸውን የፈቱ 32፣ 32 ተማሪዎችን ለናሙናነት በመውሰድ በእነሱ ላይ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ይህም ማለት የሙካራ ቡድኑ 32 ተማሪዎች ሲሆኑ የቁጥጥር

ቡድኑም 32 ተማሪዎች ናቸው፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው ተቀራራቢ በመሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የተለየው በቀላል የእጣ ዘዴ ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁለት መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ይህም አንብቦ የመረዳት ፈተናና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1ፈተና

የአንብቦ መረዳት ፈተና የዚህ ጥናት አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት እና የማጠቃለል ብልሀት ውጤትን መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የአንብቦ መረዳት እና የማጠቃለል ብልሀት ፈተናው ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ፈተናና ድህረ ትምህርት ፈተና መስጠትናውጤቶችን መመዝገብ፣ እንዲሁም በተጠኝነት የተያዙት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከመማራቸው በፊት ያለውንና ከተማሩ በኋላ የሚኖረውን የአንብቦ መረዳት በማጠቃለል ብልሀት ማየት ነው፡፡ በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች አንድ ፈተና በቅድመ ትምህርትና አንድ ፈተና በድህረ ትምህርት እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መሰረት አድርጎ በአጥኚው ተዘጋጅቷል፡፡

የተዘጋጀውም ፈተና የማንበብ ክህሎትን ይኸውም የማጠቃለል ብልሀትን በመጠቀም ለመፈተሽ የሚያገለግል ነው፡፡ የቅድመ ትምህርት የማንበብ ፈተና የተዘጋጀው የተማሪዎችን የቅድመ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል የማጠቃለል ብልሀትን ለመፈተሽና ለማየት ሲሆን የድህረ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናው የተዘጋጀው ደግሞ የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክህሎት የማጠቃለል ብልሀትን በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት እና ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ልዩነት ለማየት ነው፡፡

ሁለቱም ፈተናዎች የተዘጋጁት አጠቃላይ የምንባብ ሀሳብን፣ ከምንባቡ የሚወጡ ዝርዝር ሀሳቦችን ባካተተ መልኩ ነው፡፡ ፈተናው አስተማማኝ እና ትክክለኝነት እንዲኖረው ማለትም የቃላት ግድፈት፣ የዓረፍተ ነገር ውስብስብነት፣ አሻሚነት ያለው መልስ እና የቃላት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍች ባላቸው ቃላት ምክንያት እና የአፃፃፍ ግድፈት ምክንያት የሚፈለገውን መልዕክት ሳያስተላልፍ እንዳይቀር ለአቻ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ካሉ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ቀርቧል፡፡ ከዚያም ከተፈታኝ ተማሪዎች በሚገኝ መረጃ ጥያቄው ከላይ የተዘረዘሩትን

ችግሮች የሚኖሩት ከሆነ ተማሪዎች ጥያቄውን እንዲከቡት እና ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡ ከወረቀቱ የታችኛው ህዳግ ላይ እንዲፅፉ ቦታ ተትቶላቸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም አስተማማኝነቱ ተፈትሹዋል፡፡ ይህም ዘዴ የቅድመ ሙከራ ጥናት ይባላል፡፡ ይህን ፈተና ከላይ የቀረበውን ሂደት ካጠናቀረ በኋላ የተዘጋጀው ፈተና በአማካሪ ከተገመገመና አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመጨረሻም የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሦስት መምህራን አማካይነት ታርሞ የሦስቱን አማካይ ውጤት በመውሰድ ለውጤት ትንተናው አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

በጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋለው ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ሲሆን ዓላማውም የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ግለ-ግምገማ ለማወቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቁ አምስት ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆን የጠያቂውን ግለ-ሀሳባዊነት /subjectivity/ ለመቀነስ በአይነታቸው ነፃ ጥያቄዎች ሆነው ቀርበዋል፡፡

የቃለ መጠይቆቹን ትክክለኝነት (validity) ለማረጋገጥ ሲባልም ጥያቄዎቹ ከተዘጋጁ በኋላ ምርምሩ በሚካሄድበት አካባቢ የቋንቋ መምህራንን በማሳየትና ሀሳባቸውን በመቀበል ጥያቄዎችን የሚፈለገውን ባህሪ ለመለካት እንዲያስችሉ ተፈላጊው ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ ለዋናው ጥናት ከመዋላቸው በፊት በጥናቱ ላልተካተቱ ሶስት መምህራን ላይ ተሞክረው የሀሳብ ግልጽነታቸው፣ የቋንቋ ቀላልነታቸውና ተፈላጊውን መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ መሆናቸው ተረጋግጦ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ በተመረጡ አራት መምህራን የዋናውን ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ስራ ላይ ውሏል፡፡ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው የሚያውክ ድምጽ በሌለበት ክፍል ሲሆን እያንዳንዱ ተጠያቂ በአማካይ 15 ደቂቃ ወስዷል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት ፈተናየተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች፣ በአግባቡ ተደራጅተው፣ የማጣራት ስራ ከተከናወነ በኋላ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት በማጠቃለል ብልሀት መቅረቡ በአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸው ላይ የሚያሳየውን መሻሻል በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ ውጤቶችን ለማነፃፀር

ዳግም ልኬታ ቲ- ቴስት (Repeated Measures t-test) ቀመር አማካይነት ተሰልቷል፡፡ መረጃዎቹም በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል፡፡

## 3.5 የጥናቱ ሂደት

የጥናቱ ሂደት ተገቢ የሆነውን መንገድ እንዲከተል በመጀመሪያ ለጥናት የተመረጠው ትምህርት ቤት በመገኘት በታላሚ ናሙና የተለዩትን ክፍሎች ከመምህራን ፈቃድ ወስዷል፡፡ በቀጣይ ለዚህ ጥናት የተመረጡትን ተማሪዎች በአካል በመገኘት በቀጣይ የመማር ማስተማር ሂደት በመማር ማስተማሩ ክፍለ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር እንደመጣ በመግለፅና ዓላማውን በግልፅበማስረዳት ወደተግባር ገብቷል፡፡ በቀጣይም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ የሆነውን ፈተና ጥያቄ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ጥያቄ የቅድመ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ ከዚያም የተዘጋጁት ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥ የዚህ ጥናት አማካሪን የተዘጋጁትን ምንባቦችና ጥያቄዎች በማስገምገምና በተጨማሪም በሚሰጡ አስተያየቶች መሰረት ከአጋር መምህራን ተጨማሪ ግብዓት በመውሰድ ማሻሻያ በማድረግ ለፈተና ቀርበዋል፡፡በዚህ ጊዜ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ተመሳሳይ በሆነ ጊዜና የጊዜ ርዝማኔ በተመሳሳይ ጊዜ ተሰጥተዋል፡፡ ከዚያም የፈተና ወረቀቶቹ ተሰብስበው በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ታርሞ የሦስቱን መምህራን አማካይ ውጤት በመውሰድ በውጤት ትንተናው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል የሚኖራቸውን ደረጃ ለመለየት ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን የመጀመሪያው ደረጃ ከሆነው የቅድመ ትምህርት ፈተና መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በተመደበላቸው የመማር ማስተማር ሂደት በተቃራኒ ፈረቃ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ለማስተማር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አራት(4) ምንባቦችን ማለትም "ባጎረስኩት እጄን ተነከስኩ"፤ "የሴቷ መንገድ"፤ "የጉሌለው ሰካራም"እና "የሠራ ያገኛል" የሚሉትን ለማስተማሪያነት ተዘጋጅተዋል፡፡የሙከራውና የቁጥጥር ቡድኑ የመማር ማስተማሩን ትግበራ ተማሪዎቹ ከመደበኛው ክፍለጊዜያቸው በተቃራኒሁለቱም ቡድኖች ከሚያዚያ 1/2015 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ለአራት ሳምንታት አንብቦ የመረዳት ትምህርት ለሙከራ ቡድን የማጠቃለል ብልሀትን ብቻ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደት በመከተል ተምረዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የጥናቱ ዓላማ የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ሲሆንበፈተናና፣ በቃለ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን ይመስላል? የሚለው መሰረታዊ የምርምሩ ጥያቄ ተተንትኗል፡፡

## 4.2 የፈተና መረጃ ትንተና

የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና ምን ይመስላል? ለሚለው የጥናቱን የመጀመሪያ መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር ያለው ሚና ምን እንደሆነ በቅድመ ፈተናና በድህረ ፈተና በተሰበሰበው መረጃ አማካዩና መደበኛ ልይይቱ ተሰልቷል፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለመፈተሽም የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

በመጨረሻም በዳግም ልኬትና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት የተገኘውን መረጃ ለመደገፍ ወይም ለማጠናከር በነፃ ቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በገለፃ ተተንትኗል፡፡ እነዚህ ከመምህራን የተሰበሰቡ ቃለ መጠይቆች የሚያገለግሉት በዳግም ቲ-ቴስትና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት የተገኙትን መረጃዎች ለማጠናከር ነው፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ትንተና የሚደረገው በተማሪዎች መካከል የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ በመረዳት ክሂል ላይ ያለውልዩነት መኖሩንና አለመኖሩን ለመገንዘብ ነው፡፡ ይሄውም በቅድመ ትምህርት የተገኘው ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን ይተነተናል፡፡ ለዚህም በፈተና የተገኘው መረጃ ትንተና በገላጭ ስታትስቲክስና በባዕድ ናሙና ልኬት ቲ-ቴስት (Independent measure sample t-test) ተሰልቷል፡፡ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.1 እና 4.2 የተመለከተውን ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በነፃ ናሙና ገላጭ ስታስቲክስ

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 32 | 44.81 | 0.87 | 0.93 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 32 | 44.75 | 0.58 | 0.76 |

የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (44.81) ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (44.75) በ0.06በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.87) ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.58) በ0.29 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ወይም ተቀራራቢ (ተመሳሳይ) ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ገለፃ የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.06 እንደ በለጠ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው የነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.2 የሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ፈተና የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ልኬት

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | የነፃነት ደረጃ | የ‹‹ቲ›› ዋጋ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 32 | 44.81 | 110.926 | -6.205 | 0.063 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 32 | 44.75 | | | |

$P > 0.05$

(ቲ(110.926) = -6.205፤ P = 0.063)

ሠንጠረዥ 4.2 የተመለከተው የሁለቱ ናሙና ቲ-ቴስት በሁለቱም ስሌት እንደ ሚያሳየው ፈተናውን የወሰዱ 32 የሙከራ ቡድንና 32 የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በመተርጎምና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም (ቲ(110.926) = -6.205 ፤ P = 0.063)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ ከጉልህነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለመሪ ጥያቄው ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ -6.205 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.063 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት P >0.05 የጉልህነት ደረጃ ዋጋ የበለጠና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሠረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 4.3 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭ ስታትስቲክስ

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 32 | ቅድመ ትምህርት | 44.81 | 0.87 | 0.93 |
| | | | ድህረ ትምህርት | 45.91 | 0.41 | 0.64 |

የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት (45.91) ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (44.81) በ1.1 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (0.87) ከድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.41) በ0.46 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርትፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከላይ በቀረበው ገለፃ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በ1.1 እንደበለጠ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ

መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.4 እንደተመለከተው በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | የነፃነት ደረጃ | የ‹‹ቲ›› ዋጋ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 32 | ቅድመ ትምህርት | 44.81 | 54.983 | -11.606 | 0.001 |
| | | | ድህረ ትምህርት | 45.91 | | | |

P < 0.05 (ቲ(54.983) = -11.606፤ P = 0.001)

ሠንጠረዥ 4.4 የተመለከተው የሙከራ ቡድን ቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው ፈተናውን የወሰዱ 32 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በመተርጎም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም (ቲ(54.983)

= -11.606፤P = 0.001)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ ከጉልህነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለመሪ ጥያቄው ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ -11.606 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.001 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት P < 0.05 ያነሰና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንዳለው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ክሂል በማጠቃለል ብልሀት በመቅረቡ ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና

ቲ-ቴስት ተሰልቶ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (ቲ(54.983) =

-11.606፤ P= 0.001) አሳይቷል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭ ስታትስቲክስ

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ አማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 32 | ቅድመ ትምህርት | 44.75 | 0.58 | 0.76 |
| | | | ድህረ ትምህርት | 45.03 | 0.29 | 0.54 |

የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (45.03) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (44.75) በ0.28 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.58) ከድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.29) በ0.29 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ገለፃ የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.29 እንደ በለጠ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.6 እንደተመለከተው በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6 የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በጻግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | የነፃነት ደረጃ | የ‹‹ቲ›› ዋጋ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 32 | ቅድመ ትምህርት | 44.75 | 55.943 | -3.548 | 0.064 |
| | | | ድህረ ትምህርት | 45.03 | | | |

p> 0.05 (ቲ(55.943) = -3.548፤ P = 0.064

ሠንጠረዥ 4.6 የተመለከተው የቁጥጥር ቡድን የቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው ፈተናውን የወሰዱ 32 የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በመተርጎምና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም (ቲ(55.943) = -3.548፤ P = 0.064)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ ከጉልህነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለመሪ ጥያቄው ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡ የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ -3.548 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.064 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቀረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ የበለጠና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌላቸው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 4.7 የሙከራዊ ቡድንና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በነፃ ናሙና ገላጭ ስታትስቲክስ

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት | መደበኛ አማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|
| የድህረ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 32 | 45.91 | 0.41 | 0.64 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 32 | 45.03 | 0.29 | 0.54 |

የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (45.91) ከቁጥጥር ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (45.03) በ0.88 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራ ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.41) ከቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.29) በ0.12በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የሁለቱም ቡድኖች ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤት ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት አለው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ገለፃ የሙከራ ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.88 በከፍተኛ ደረጃ እንደበለጠ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግንድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ4.8 እንደተመለከተው የነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.8 የሙከራዊ ቡድንና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ልኬት

| የፈተና አይነት | የሙከራ ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | የነፃነት ደረጃ | የ‹‹ቲ›› ዋጋ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የድህረ ትምህርት ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 32 | 45.91 | 110.926 | -8.949 | 0.001 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 32 | 45.03 | | | |

P < 0.05 (ቲ(110.926) = -8.949፣ P = 0.001)

ሠንጠረዥ 4.8 የተመለከተው የሁለቱ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በመተርጎምና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም (ቲ(110.926) = -8.949፣ P = 0.001)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ ከጉልህነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለመሪ ጥያቄው ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡ የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ -8.949 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.001 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት መኖሩን ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ

ቡድኖች አንብቦ መረዳት ክሂልን በማጠቃለል ብልሀት መቅረቡ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ የውጤት መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

## 4.3. የቃለ መጠይቅ መረጃ ትንተና

በቃለመጠይቅውይይትየተሰበሰቡትመረጃዎችየአማርኛቋንቋመምህራንየማጠቃለልብልሃት ለአንብቦመረዳትያለውፋይዳምንይመስላል?
የሚለውንየምርምሩንጥያቄመሰረትአድርጎእንደሚከተለውተተንትነዋል፡፡በቃለመጠይቁበ መጀመሪያለተጠያቂዎችየቀረበው
አንደኛውጥያቄየንባብክሂልንሲያስተምሩአዘውትረውየሚጠቀሙትየትኛውንየንባብሂደትነ ው? ለምን? የሚልሲሆንአራቱምመምህራንሦስቱንየንባብሂደትማለትምቅድመ-ንባብ፣ሂደት- ንባብእናድህረንባብሂደቶችንእንደሚከተሉገልፀዋል፡፡

ሁለተኛውቃለመጠይቅበንባብክሂልትምህርትጊዜለማስተማርቀላልነውብለውየሚያስቡትሂ ደትየትኛውነው?
ለሚለውጥያቄሦስቱመምህራንበመማርማስተማርሂደትበማንበብክሂልቀላልናከባድየሚልደረ ጃአለመኖሩንጠቁመዋል፡፡

አንድ መምህርደግሞየሚቀጥለውን ብለዋል፡፡በንባብክሂልትምህርትጊዜለማስተማርቀላልነውብዬየማስበውቅድመ-ንባብሂደትንነውካሉበኋላምክንያቱንሲገልፁበቅድመ-ንባብሂደትጊዜተማሪዎችየቅድመእውቀታቸውንተጠቅመውሀሳባቸውንየሚሰነዝሩበትናለንባ ብሂደቱየሚዘጋጁበትሲሆንከባድሂደትየምለውደግሞሂደት-ንባብንነውብለዋል፡፡ምክንያቱንሲገልፁምተማሪዎችበአብዛኛውእንዲያነቡየማደርገውበግል በመሆኑፈጣንተማሪዎችቀድመውአንብበውከጨረሱበኋላትዕዛዜንባለመስማትቀጣዩንአንቀፅ ማንበብስለሚጀምሩናእኩልስለማይጨርሱበእኩልለማስሄድከባድነውብለዋል፡፡ድህረንባብግ ንሁሉምከጨረሱበኋላየሚፈጸምበመሆኑአስቸጋሪአይደለምብለዋል፡፡የእኚህመምህርሂደትን ባብላይየሚሰጡትንመማሪያወይምመፅሐፍላይያለውንትዕዛዝበአግባቡአላስተላለፉም፡፡መል ዕክቱንየማስተላለፍድክመትእንዳለባቸውያሳያል፡፡

ሦስተኛውቃለመጠይቅደግሞበመማርማስተማርሂደትየማንበብክሂልንሲያስተምሩየተማሪዎ ችየማጠቃለልብልሃትምንይመስላል?
ለሚለውጥያቄአራቱምመምህራንሲመልሱየተማሪዎችየማጠቃለልብልሃትለማንበብካላቸው ፍላጎትአንፃርየሚወሰንሲሆንለምንባብትኩረትሰጥተውየሚያነቡተማሪዎችየምንባቡንሀሳብተ

ረድተውየማጠቃለያሀሳብለመስጠትእንደማይቸገሩነገርግንለምንባቡትኩረትየማይሰጡትግ ንየምንባቡንየማጠቃለያሀሳብመፃፍወይምመናገርእንደማይችሉገልፀዋል፡፡

አራተኛውቃለመጠይቅየተማሪዎችየንባብፍላጎት (የማጠቃለልብልሃት) የመማርፍላጎትበመምህሩጥረትናአቀራረብይወሰናልብለውያምናሉ? ለሚለውጥያቄአራቱምመምህራንሲመልሱበመማርማስተማርሂደትየማጠቃለልብልሃትበመ ምህራንየትምህርትአሰጣጥአንፃርየሚወሰንሳይሆንበተማሪዎችፍላጎትየሚወሰንናየሚለካመሆ ኑንአመላክተዋል፡፡

አምስተኛው ቃለ መጠይቅ በመማር ማስተማሩ ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ ተማሪዎች የበለጠ ምንባቡን የሚረዱት በየትኛው ብልሀት ሲማሩ ነው? ለሚለው ጥያቄ አራቱም መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ ተማሪዎች የበለጠ ምንባቡን የሚረዱት በየትኛው ብልሀት ሲማሩ እንደሆነ አለመለየታቸውን ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይበቃለመጠይቁየማጠቃለልብልሃትለአንብቦመረዳትበመማርማስተማርሂደቱበማ ንበብክሂልቀላልናከባድየሚባልደረጃአለመኖሩንጠቁመዋል፡፡በተማሪዎችየማጠቃለልብልሃ ትለማንበብካላቸውፍላጎትአንጻርየሚወሰንመሆኑንአመልክተዋል፡፡ከዚህበተጨማሪበመማር ማስተማርሂደትየማጠቃለልብልሃትበመምህሩ/ሯ/ የትምህርትአሰጣጥየሚወሰንሳይሆንበተማሪውፍላጎትየሚወሰንናየሚለካመሆኑንአመልክተዋ ል፡፡

## 4.4 የውጤት ማብራሪያ

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና በተሰበሰቡት መረጃዎች በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል የአንብቦ መረዳት ክሂልን በማጠቃለል ብልሀት መቅረቡ ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር ሊኖረው የሚችለውን አስተዋፅኦ ለመመርመር መረጃዎች በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክሶች ተተንትነዋል፡፡

የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (44.81) ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (44.75) በ0.06በልጦ መስተዋሉን ቀደም ሲል በሰንጠረዥ 4.1 ስር ተገልጿል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (0.87) ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (0.58) በ0.29 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ

ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ወይም ተመሳሳይ መሆኑን ከስሌቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመካከላቸው ላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው የነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት ተሰልቶ የተገኘው የሚከተለውን ያሳያል፡፡ ሠንጠረዥ 4.2 የተመለከተው የሁለቱ ናሙና ቲ-ቴስት በሁለቱም ስሌት እንደ ሚያሳየው የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ -6.205 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ደግሞ 0.063 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ የበለጠና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሠረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፈተና አማካይ ውጤት (45.91) ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (44.81) በ1.1በልጦ መስተዋሉን በሠንጠረዥ 4.3 እና 4.4 ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.87) ከድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.41) በ0.46 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከላይ በቀረበው ገለፃ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በ1.1 እንደበለጠ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ የሙከራ ቡድን ቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን በሰንጠረዥ 4.4 ተመልክቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ $P < 0.05$ (ቲ(54.983) = -11.606፤ $P = 0.001$) ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንዳለው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂልን በማጠቃለል ብልሀት በመቅረቡ ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (45.03) ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (44.75) በ0.28 በልጦ መገኘቱን በሰንጠረዥ 4.6 ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.58) ከድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.29) በ0.29 በልጦ መጠነኛ ልዩነት ማሳየቱን ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ በመጠቀም በጻግም ልኬት ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው $p < 0.05$ (ቲ(55.943) = -3.548፣ P = 0.064 ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድን የቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ የበለጠና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌላቸው ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (45.91) ከቁጥጥር ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (45.03) በ0.88 በልጦ መገኘቱ በሰንጠረዥ 4.7 ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.41) ከቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልዩነት (0.29) በ0.12በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የሁለቱም ቡድኖች ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤት ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት አለው ማለት ይቻላል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ በመጠቀም የተሰላው የሁለቱ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በመተርጎምና ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚከተሉት ደረጃዎች ተቀምጠዋል፡፡ ይኸውም (ቲ(110.926) = -8.949፣ P = 0.001) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ-ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልህነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካይ ውጤታቸውንና መደበኛ ልዩነታቸውን ስንመለከት

የጎላ ልዩነት መኖሩን ስሌቱ ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂልን ማስተማር በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ የውጤት መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ሲታይ የሙከራ ቡድኑ አንብቦ መረዳትን በማጠቃለል ብልሀት ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ የበለጠ ነው፣ የሚል አንድምታ አለው፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ መገኘቱ አንድ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጥናት የሙከራ ቡድኑ ያላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥሩ ነው፣ የሚል አንድምታ አለው፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ መገኘቱ አንድ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት ችሎታ ከቅድመ ትምህርት ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በዋናነት በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ አላቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንብቦ የመረዳት ክሂልን በማጠቃለል ብልሀት ማስተማር ምክንያት የአንብቦ መረዳት ክሂላቸው ምን ያህል መዳበር ይችላል? የሚለውን ሀሳብ ስንመለከት በሙከራ ቡድኑ ውጤት መሰረት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸው በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን ውጤት ከምሁራን ሀሳብ አንፃር እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

በአጠቃልይ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተገለጸው የተለያዩ ምሁራን የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል፡፡ ለምስሌ የሚከተለውን የምሁራን ገለፃ መመልከት ይቻላል፡፡
ማጠቃለል ከቋንቋ ማስተማሪያ ብልሀቶች አንዱ ሆኖ አንድ በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበን ጽሁፍ በማንበብ ሀሳቡን በታመቁና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ነው (Oxford 1990)፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመነሻ ጽሁፍን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግንም ይፈልጋል፡፡
ማጠቃለል ማለት ዋናውን ጽሁፍ በማሳጠር በጣም አስፈላጊ ነጥቦችን፣ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ አስፈላጊ ዝርዝሮችን ብቻ የያዘ ከዋናው ጽሁፍ ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነን

ጽሁፍ ነው፡፡ በማጠቃለል አላስፈላጊ መረጃዎችን በማስወጣትና አጠቃላይ ሀሳብን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር መሆኑን Denton and etal (2007)፣ ገልፀዋል፡፡ በDentonን አገላለጽ ስድስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡- ዋና ዋና ሀሳቦችን ማስፈር፣ አስፈላጊ ነጥቦችን ማስመር፣ የሚቻሉትን ማያያዝ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ማጠቃለያውን መጻፍና ማጠቃለያውን መከለስ/ማሻሻል ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

ማጠቃለል አንድን በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍ በማንበብ ሀሳቡን በታመቀና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል ሲል Oxford (1990)፣ አብራርተዋል፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመነሻ ጽሁፉን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግን ይፈልጋል በማለትም ጭምር ገልፀዋል፡፡

አንድን ጽሁፍ ለማጠቃለል፣ የማጠቃለል ብልሀትን በመጠቀም ተማሪን ማለማመድ እንደሚቻል Armbruister and etal (2002)፣ ጠቁመዋል፡፡ ከስልቶች ውስጥ የጽሁፉን መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይ ሀሳቡን የሚያመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን ማስፈር በመሪ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር የሚካተቱ ሀሳቦችን መለየት፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀት እርከናዊ አጠቃሎ (Hierarchical summary) Tayler and Bich (1984)ን፣ Tayler and Berkoywites (1980)ን፣ በመጥቀስ Armbruister and etal (2002)፣ አስረድተዋል፡፡ በዚህም ርዕሶቹን፣ ንዑስ ርዕሶቹን እና አንቀፆቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ማዘጋጀት፣ በመቀጠልም በየርዕሶቹ፣ በየንዑስ ርዕሶቹና በየአንቀፆቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይቶ ማውጣት፡፡ በመጨረሻሻም ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሳብን በማፍለቅ በመሪው ሆሣብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሳብ መጻፍ የሚሉ ናቸው፡፡ Birawon and Diay (1983)፣ Rahert (1986)ን ዋቢ በማድረግ Armbruister and etal (2002)፣ እንደጠቀሱት አላስፈላጊ መረጃዎችን፣ የተደጋገሙ መረጃዎች ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመተካት ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ የተገለፁ ሀይለ ቃሎች ወይም ዋና ሀሳቦች ካሉ እንደ መሪ ሀሳብ አድርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀፁን ዋና ሀሳብ በሀይለ ቃል መልኩ ያላሰፈረ ከሆነ በአንባቢው በኩል የራስን ሀይለ ቃል መፍጠር ናቸው፡፡ የዚህን ጥናት ውጤት ከምሁራኑ ገለፃ አንፃር ሲታይ አዎንታዊ ግንኙነት አለው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው የታለሙት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፤

1. የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን ይመስላል?
2. የማጠቃለል ብልሀትን በመማርና ባለመማር መካከል ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ጉልህ ልዩነት ይኖረዋልን?

የጥናቱ ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በአስረኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የየምሳ አፍ ፈት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ከሚማሩ420 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጭ ናሙና የተመረጡት የ‹‹10ቢ›› እና ‹‹10ዲ›› ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ከነዚህ ተማሪዎች መካከል በታላሚ ናሙና 64 ተማሪዎችን በመምረጥ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ በጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም የምንባብ ፈተና እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

ተጠኚዎችም በመማር ማስተማሩ ሂደት በተመረጡ ምንባብ ከማስተማር በፊት የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ መለኪያ ፈተና በጥናቱ አማካሪና በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማስተካከያ ታክሎበት አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን ለመለካት “የአልኮል ሱሰኝነት” በሚል የምንባብ ርዕስ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመቀጠልም ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ማስተማሪያ ጽሁፎች ለአራት ሳምንት ወይም ስምንት ክፍለ ጊዜ ሲማሩ ቆይተዋል፤ በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና “የኮረና ቫይረስ” በሚል ምንባብ ርዕስ ፈተናውን ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በፈተና አማካኝነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ በዋናነት የዚህ ጥናት ጉዳይ የሆነውን የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር ሊኖረው የሚችለውን አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ ለመመርመር በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ

ትምህርት ፈተና የተገኘውን መረጃ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም የቅድመ ትምህርት ፈተና በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖች ላይ አማካይ ውጤቶች መካከል በስታትስቲክስ ምንም ልዩነት ያልታየበት በመሆኑ ለመማር ማስተማሩ የተመረጡት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸው ተመሳሳይ መሆኑንና ለጥናቱ መነሻ የሚሆን በመሆኑና ለማስተማር የሚያስችል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ክፍል የታየው በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው መረጃ ትንተና እንደሚያሳየው ይህ ጥናት በመጀመሪያ ይዞት የተነሳው መሪ ጥያቄ የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን ይመስላል? የማጠቃለል ብልሀት በመማርና ባለማስተማር መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታጉልህ ልዩነት ይኖረዋልን? የሚል ነበር፡፡ በቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት መረጃ መሰረት በተሳታፊዎች የቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት አማካዮች መካከል በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት መሰረት በስታትስቲክስ ጉልህ ($p < 0.05$) ልዩነት ታይቷል፡፡ በዚህም በሙከራዊ ቡድኑ የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ትንተና መሰረት የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር ሊኖረው የሚችለውን አስተዋፅኦ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ ይልቅ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የተሻለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ ላይ አስተዋፅኦው የጎላ እንደሆነ ያሳያል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

ሀ.የማጠቃለል ብልሀትን ለአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያነት መጠቀም ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር አስተዋፅኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር ላይ የማጠቃለል ብልሀት አስተዋፅኦ አለው የሚል እንድምታ አለው፡፡

## 5.3 አስተያየት

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም የተማሪዎችን በማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር እንዲቻል የሚከተለው አስተያየት ተጠቁሟል፡፡

- መምህራን በማጠቃለል ብልሀት በመጠቀም ማስተማር ለአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለው ተገንዝበው፣ አንብቦ የመረዳት ክሂልን በማጠቃለል ብልሀት ቢያስተምሩ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


መሪነሽ ፀጋዬ፡፡ (2002)፡፡ "የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልታተመ፡፡

ሙሉገበያ ያለው (2009)፡፡ "የጽሁፍአወቃቀርንማስተማርአንብቦየመረዳትንችሎታበማጎልበትረገድያለውሚና፡ ፡"በአዲስዘመንከፍተኛ 2ኛደረጃትምህርትቤትበዘጠነኛክፍልተማሪዎችተተኳሪነት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተማርስ ዲግሪማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ማስተዋል ውበቱ (1989)፡፡ "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛየአንብቦመረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡" አዲስ አበባዩኒቨርሲቲ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡

ሠርካለም ይገረሙ (2010)፡፡ "እእምሮአዊ እና ልእለአእምሮአዊ የማንበብብልሀቶችአማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ" በሰንዳፋ ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤትተተኳሪነት፡፡ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ባንቺአምላክ ፈጠነ (2013)፡፡ "አዕምሯዊ የመማር ብልሀቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦየመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ ፤ በሰባተኛ ክፍልተማሪዎችተተኳሪነት "፡፡

ተስፋ ወልደሚካኤል፡፡ (2001)፡፡ "የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦየመረዳት ችሎታ በተመረጡ የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ያልታተመ፡፡

ታምሩ ፀጋዬ፡፡ (2008)፡፡ "በበርትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ፤ ጸታ ተኮር ጥናት፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልታተመ፡፡አስረኛ ክፍል የአማርኛቋንቋ ትምህርት የተማሪው መጽሐፍ (2004)፡፡ አዲስአበባ፡፡

እሱባለው ወልደገብረኤል (2010)፡፡ "የማንበብ ብልሀትን በግልጽ ማስተማርአንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሀትሽግግሮሽ ያለውአስተዋፅኦ" በሱማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሱማልኛ ቋንቋ አፍ

ፈትተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሚያ የቀረበጥናት፡፡

እንድሪስ አባይ (2009)፡፡ "በቴክስት ውቅር ብልሀቶች በአማርኛ ማንበብንመማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ በስድስተኛክፍልተተኳሪነት፡፡" አዲስ አበባዩኒቨርሲቲ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡

ከድር ሰይድ፡፡ (2009)፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሀ ትምህርት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ፅሁፍ፡፡ ጅማዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልታተመ፡፡

ያለውእንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡የምርምርመሰረታዊመርሆዎችናአተገባበር፡፡ አዲስአበባ፣ንግድማተሚያቤት፡፡

ገብረመድን ተስፋው፡፡ (2011)፡፡ "የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውሚና፣ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ2ኛደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪማሚያ የቀረበ ፅሁፍ ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልታተመ፡፡

ማንቢቱ ዲበኩሉ፡፡ (2010)፡፡ "ልእለ ግንዛቤ የማንበብ ብልሀቶች አጠቃቀምከማንበብ አመለካከት እና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ"በቆላ ድባሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መነሻነት፡፡"ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት፡፡

Block, Cand Mangieri,J.(1995).Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature,Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion.

Brown, H. (1994). Teaching by Principles: An InteractiveApproach to LanguagePedagogy.Englewood Cliffs, NJ: Prentice Hall Regents.

Campbell, J., Kelly, D., Mullis, I.V.S., Martin, M.O., & Sainsbury, M. (2001).

Framework and specifications for PIRLS assessment2001, second edition.Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Conley, Mark W. (1997).Reading and Writing: teaching for the connection.(2nd ed.)Less har court Brache and company.

Fox, E., & Alexander, P. A. (2009). Text Comprehension: A Retrospective, Perspective, and Prospective. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), Handbook of Research on ReadingComprehension(pp. 227-239).New York: Routledge.

Grellet,F.(1991).Developing reading skills.Cambridge:Cambridge unverstiy Press.

Janan, D. (2011). "Towards a New Model of Readability".Doctorial Dissertation University of Warwick institutionalrepository:http://go.warwick.ac.uk/wrap.

Leslie, L., & Cladwell, J. (2009).Formal and Informal Measures of Reading Comprehension. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), Handbook of Researchon ReadingComprehsion(pp. 403). New York: Routledge.

Lindsay and knight.(2006).Learning and teachingEnglish:Acourse for teachers.Oxford: oxford university press.

Madsen, H.S.( 1983). Techniques in Testing. Oxford: Oxford: Oxford University Press

Nunan, D. (1989). Language Teaching Methodology: A Textbook for Teachers.London: Prentice Hall.

…………… (1991). Language Teaching Methdology a Textbookfor Teachers.New York: Prentice Hall Inc.

Nuttall, C. (1982). Teaching reading skills in a foreign language. London: Heinemann.s

…………(1996).Teaching reading skillsin a foreignlanguage: oxford. Macmillan Publishers limited.

O'Malley, J. M. and Chamot, A. U. (1995).Learning Strategies in SecondLanguage Acquisition.Cambridge, UK: Cambridge University Press.

Oxford, R. L. (1990). Language Learning Strategies: what Every TeacherShould Know.Boston: Heinle & Heinle Publishers.

Raimes, A. (1983). Techniques in teaching writing. Oxford: Oxford
University press Inc.

Smith, F. (1985).Reading.Great Britain Cambridge university pressStahl, S. A. (1998). Understanding Shifts in Reading and Its Instruction. Peabody Journalof Education, 73(3/4), 31-67.

Vaughn, Sharon R.(2012). Strategies for Teaching Students with Learningand BehaviorProblems. New Jersey: Pearson Education.

Walcutt, C. C. (1967). Reading A Professional Definition. The ElementarySchool Journal, 67(7), 363-365.

Williams,(1990).Reading in the Class room. London:Macmillan Publishers Ltd.

# አባሪዎች

## አባሪ "1"፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

**ቅድመ ትምህርት ፈተና**

የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸውን ለመመርመር የሚያገለግል ፈተና

መለያ ቁጥር .........

ክፍል .........

የተፈቀደው ጊዜ፡- 1፡30

**አጠቃላይመመሪያ፡-**

የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማጠቃለል ብልሀት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት በመረዳት፤ የምንባቡን ሀሳብ በራስ አገላለጽ ለመግለጽ የሚያስችሉ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ፣ በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

## ምንባብ

## የአልኮል ሱሰኝነት

የአልኮል ሱሰኛ የሆንኩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለሁ ነበር። በእርግጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመዝናናት ይጠጣሉ። ነገር ግን መጠጥ ቤት ሄጄ የምጠጣው ለመዝናናት አልነበረም። እኔ የምጠጣው ለመመሳሰል ነበር። ከፍተኛ የሆነ ከማህበረሰቡ ጋር የመቀላቀል ፍርሃት ችግር ስለነበረብኝ ከመኝታ ቤት ለቅቄ መውጣት ይከብደኛል። ጓደኛ ለማፍራት ምንም በራስ መተማመን አልነበረኝም። የሚወዱኝ ቤተሰቦች እና ጓደኞች እንዳሉኝ ባውቅም ሁልጊዜ ብቸኝነት ይሰማኝ ነበር። ራሴን እጠላለሁ። አልኮል ለጥቂት ሰዓታምቢሆን በራሱ የሚተማመን እና ተግባቢ ሰው ወደመሆን የሚቀይረኝ መጠጥ ነው። ጽኑ ህመሜን ያደነዝዘዋል። ለሁለት አመት ያህል አልኮል በፍፁም ያልጠበኩት መድሃኒቴ ሆነ።

ነገር ግን የአልኮል ሱስ የሚያስከትለውን አሰከፊ ችግር እንደ እራስን መጥላት፣ እራስን መራገም ከፍተኛ የሆነ ፀፀት ውስጥ መግባት ወዘተ. በመረዳት ከአልኮል ሱስ ለመላቀቅ ስጋፈጥ ቁም ስቅሌን አየሁኝ። እራሴን ትሁት ለማድረግ፣ ለመስማት እና ከእኔ በባሰ ችግር ውስጥ ያለፉ ሰዎችን ምክረ ሀሳብ ተቀበልኩ። ለክፉ ቀን ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ግልፅ በመሆን አወያየኋቸው። ከሰዎች ጋር በመገናኘት በግልፅ የማስበውን በመናገር፣ በምን እንደምቸገር በመግለፅና ማንም ሰው ስለእኔ ሲጠይቀኝ እውነቱን መናገር ጀመርኩኝ። ያለብኝን ከፍተኛ የሆነ ከማህበረሰቡ ጋር የመቀላቀል ፍርሃት ችግር እንዲቀረፍልኝ የስነልቦና ህክምና እንዲደረግልኝ ጠየኩኝ። ሀሳበ ግትር ከመሆን ይልቅ በማውራት፣ በማሰብና እራሴን እንደጠቃሚ ሰው በመውሰድ ችግሮቼን ተጋፈጥኳቸው፤ እራሴን በእውነት ለመውደድ ተማርኩኝ። ለራሴ ችግር ፈቺ ሆንኩኝ። በመጨረሻም ከአልኮል ሱስ መላቀቅ ቻልኩኝ።

ምንጭ፡- https://gemenaye.com/ alcohol-addiction

**ትእዛዝ፡-** ምንባቡንመሠረትበማድረግለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. ባለታሪኩ መጠጥ የሚጠጣው ለምንድን ነበር?

………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………

2. ባለታሪኩ አልኮል መጠጥ መጠጣት የጀመረው መቼ ነው?

………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………

3. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አልኮል መጠጥ የሚጠጡት ለምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………

4. ባለታሪኩ ከአልኮል ሱስ መላቀቅ የቻለው እንዴት ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………

5. ባለታሪኩ "እራሴን እጠላለሁ" ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………

6. ባለታሪኩ ችግሩን ያወያየው ለማን ነው?

…………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………

7. "ለራሴ ችግር ፈቺ ሆንኩኝ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

…………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………

8. ባለታሪኩ ምክረ ሀሳብ የተቀበለው ከማን ነው?

…………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………

9. ምንባቡን በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

……………………………………

10. የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት በአጭር ግለፁ፡፡

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

## አባሪ "2"፡- የድህረ ትምህርት ፈተና

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

**የድህረ ትምህርት ፈተና**

የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸውን ለመመርመር የሚያገለግል ፈተና

መለያ ቁጥር .........

ክፍል .........

የተፈቀደው ጊዜ፡- 1፡30

**አጠቃላይመመሪያ፡-**

የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማጠቃለል ብልሀት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት በመረዳት፤ የምንባቡን ሀሳብ በራስ አገላለጽ ለመግለጽ የሚያስችሉ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ፣ በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

ምንባብ

# የኮሮና ቫይረስ

የኮሮና ቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) SARS-CoV-2 በሚባል ቫይረስ አማካኝነት የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ነው። ቫይረሱ ሰዎችን እና አንዳንድ እንስሳትንም የሚያጠቃ በሽታ ሲሆን በማስነጠስ፣ በማሳል፣ በመናገር፣ ወቅት በሚወጡ ጠብታዎች ከሰው ወደሰው ወይም ከእንስሳት ወደ ሰው ይተላለፋል። በቫይረሱ የተያዙ አብዛኛዎቹ ሰዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ የመተንፈሻ አካላት ህመም ቢያጋጥማቸውም ልዩ ህክምና ሳያስፈልጋቸው ይድናሉ። ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ በጠና ይታመማሉ። ስለሆነም የተለየ የሕክምና ክትትል ያስፈልጋቸዋል። በተለይም በዕድሜ የገፉ ሰዎች፣ የልብና የደም ቧንቧ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣ ሥር የሰደደ የመተንፈሻ አካላት በሽታ ወይም እንደካንሰር ያሉ ሥር የሰደዱ በሽታዎች ያሉባቸው ሰዎች ለከባድ ሕመም የመጋለጥ

ዕድላቸው ሰፊ ነው። ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው በኮቪድ-19 በጠና ሊታመም ወይም በማንኛውም እድሜ ሊሞት ይችላል።

የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል እና ለማዘግየት የተሻለው መንገድ ስለበሽታው እና ቫይረሱ ሥርጭት ጠንቅቆ ማወቅ ነው። ከእነዚህም ውስጥ ከሌሎች ቢያንስ የአንድ ሜትር ርቀት ራስን መራቅ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛን በትክክል መጠቀም፣ እጅን በሳሙና መታጠብ፣ እና ሳንታይዘር መጠቀም ናቸው። እነዚህን በማድረግ እራስን እና ሌሎችን ከበሽታው መጠበቅ ይቻላል። በተጨማሪም ክትባት በመከተብና የኮቪድ-19 መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ሌላኛው የመከላከያ መንገድ ነው። በበሽታው ከተያዘ ሰው አፍ ወይም አፍንጫ ውስጥ በሚያስሉበት ጊዜ፣ በሚናገሩበት ጊዜ፣ በሚዘፍኑበት ወይም በሚተነፍሱበት ጊዜ በትንሽ ፈሳሽ ቅንጣቶች ውስጥ ሊሰራጩ የሚችሉ ጠብታዎች ስላሉ የአተነፋፈስ ስነ-ምግባርን መለማመድ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በክንድ አፍን በመሸፈን መሳልና ማስነጠስ፣ ሕመሙ የተሰማው ሰው ከበሽታው እስኪያገግም ራሱን በማግለል ቤት ውስጥ መቆየት ሁነኛ መፍትሔ ነው።

**ትእዛዝ፡-** ምንባቡንመሠረትበማድረግለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. ኮቪድ-19 ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………

2. ቫይረሱ የበለጠ የሚያጠቃው ማንን ነው?

…………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………

3. በሽታው የሚተላለፈው እንዴት ነው?

…………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………

4. በሽታውን የመከላከያ መንገዶች ምንድን ናቸው?

…………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………

5. በበሽታው የተያዘ ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች ምንድን ናቸው?

…………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………

6. የመጀመሪያው አንቀጽ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………

……………………………………………………

7. የሁለተኛው አንቀጽ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………

8. ቫይረሱ ከሰው ውጪ የሚያጠቃው ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………

9. ምንባቡን በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

10. የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት በአጭሩ ግለፁ፡፡

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

## አባሪ "3"፡- የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

ውድ መምህር ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ ሆነው ስለተገኙ ከልብ እያመሰገንኩ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከመማር ማስተማሩ ሂደት አንፃር የሚስማማዎትን መልስ ይስጡ፡፡

1. የንባብ ክሂልን ሲያስተምሩ አዘውትረው የሚጠቀሙት የትኛውን የንባብ ሂደት ነው? ለምን?

2. በንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ለማስተማር ቀላል ነው ብለው የሚያስቡት ሂደት የትኛውነው?

3. በመማር ማስተማሩ ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ምን ይመስላል?

4. የተማሪዎች የንባብ ፍላጎት (የማጠቃለል ብልሀት) የመማር ፍላጎት በመምህሩ ጥረትናአቀራረብ ይወሰናል ብለው ያምናሉ?

5. በመማር ማስተማሩ ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ ተማሪዎች የበለጠ ምንባቡንየሚረዱት በየትኛው ብልሀት ሲማሩ ነው?

## አባሪ "4"፡- የማስተማሪያ ጽሁፎች

## ትምህርት አንድ

የትምህርቱ ርዕስ፡- ምንባቡን አንብቦ በመረዳት የመፃፍ ክሂል መለማመጃ ጥያቄዎችን መስራት

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የምንባቡን ሀሳብ በመረዳት ለመፃፍ ክሂል መለማመጃ የቀረቡ ጥያቄዎችን በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፣
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በራሳችሁ አገላለፅ ትገልፃላችሁ፣

**ምንባብ**

**"ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ"**

- .ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. አሁን የምናነበው የምንባብ ርዕስ ምን ይላል?
2. ‹‹ ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ›› የሚለው ርዕስ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኃል?

- የንባብ ጊዜ

ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ባበዳሪ እና በተበዳሪ መካከል የተፈጠረውን ነገር ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

**"ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ"**

ከብዙ አመታት በፊት አቶ ሞልቶት የሚባል አንድ ሀብታም ሰው በሸዋ ይኖር ነበር፡፡ ይህም ሰው የበለጸገና ትህትና ያለዉ ሰው በመሆኑ ብዙ ሰዎች ያከብሩትና ይፈሩት ነበር፡፡ ከደግነቱም ብዛት የተነሳ ለሰዎች ያላራጣ ገንዘብ ያበድር ነበር፡፡ ድሆች ጎረቤቶችን ያግዝ ነበር፡፡

አንድ ተንኮለኛ ሰዉ ገንዘቡን ተበድሮ እየተሰወረ ሲኖር ከዕለታት አንድ ቀን ለጉዳዩ ወደ አደባባይ ወጥቶ ሳለ ሰዉዬዉን በድንገት አገኘዉ፡፡ ተበዳሪዉም እስካሁን ድረስ ረስቶት

ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለገንዘቡ አይጠይቀኝም እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳምና ሃብታሙ ተበዳሪዉን በሰላም ካነጋገረው በኃላ በስውር ማመልከቻ ጽፎ ከሰሰው፡፡ ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል እንደተባለው ሁሉ ይህ ባለፀጋ ባጠገቡ ሳለ ወዲያው ጉዳዩን እንደፈጸመ ሳይጠይቀው ቆይቶ አሁን ተረስቶ በነበረው ገንዘብ ሊዛለል ነው፡፡ ተበዳሪዉም ምን ያምጣ ድሃ ምን ያግሳ ውሀ የሚባለዉን ተረት እያሰላሰለ ‹‹ መበደሩንስ ተበድሬ ነበር ነገር ግን አሁን የምከፍለዉ የለኝም ብዬ ለዳኞች ብነግራቸዉ አንድ አስተያየት ያደርጉልኛል፡፡›› በማለት ተስፋ አደረገ፡፡

እንደዚሁበዳኛው ፊት ቀረበና ሲጠየቅ አመነ፡፡ ይሁን እንጂ ምንም የሌለዉ መናጢ ድሀ መሆኑን ለዳኞች አመለከታቸው፡፡ ዳኞቹም ፍርድ አያውቅ ዳኛ ተገን አያዉቅ እረኛ እንደተባለዉ ያሉ ነበሩና እስከዛሬ ድረስ ከቆየስ አሁን ልትጠይቀዉ አይገባህም ብለው በሃብታሙ ላይ ፈረዱበት፡፡ በዚህ ነገር አቶ ሞልቶት ተናዶ ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ ብሎ በመናገር በአዕምሮዉ እያመላለሰ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ አቶቢሰውር ሊጠይቀው ቢመጣ ሲናደድ እና ሲበሳጭ አገኘው፡፡ እሱምጥቅትትዕግስትእንዲያደርግከነገርከፉቁጭትካዉሬከፉድርጭትየተባለውንተረትከዚህ በፊትአልሰማህምን? ባይሆንስእንዴትእስከዚህድረስትበሳጫለህአይሆንም! ከቶእንደዚህያለስራእንዳይደግምህስለዚህለወደፊቱአባትካነሰዉምግባርያነሰዉየተጎዳናየተበ ላሸመሆኑንእያሰብክገንዘብህንአታበድርብሎ መከረው፡፡ከዚህበኃላአቶሞልቶትለካሰዶማሳደድሲያምርህዶሮህንበቆቅለውጥተብሎየተነገረ ዉይህንየመሰለችግርለሚገጥማቸውሰዎችኖሯልብሎከዚያ ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ማበደሩን አቋረጠ ይባላል፡፡

ምንጭ፤ (ሀዲስ አለማየሁ ተረት ተረት የመሰረት)አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ

- ❖ ድህረ ንባብ

አንድ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**I. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. አቶ ሞልቶት የተባሉት ምን አይነት ሰውናቸው?

……………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………

2. ከአቶ ሞልቶት ገንዘብ የተበደረው ብድሩን መልሷል?ለምን?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

3. አቶ ሞልቶት የተናደደዉ ለምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

4. አቶ ሞልቶት በጣም ሲበሳጭ ያጽናናው ሰዉ ማነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

**I. ከምንባቡ ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተካተዋል እነዚህን ምሳሌያዊ ንግግሮች ለይታችሁ በማውጣት በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ፡

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

- **ከምንባቡ ለወጡት ቃላት እና ለሀረጋት ተመሳሳይ ፍች መስጠት**

**I. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ ይዘት የወጡ ናቸው በ ‹‹ሀ›› ክፍል የቀረቡትን ከተመሳሳያቸው ከ‹‹ለ›› ጋር አዛምዱ፡፡**

<u>ሀለ</u>

1.መናጢ.ድሀ.ወለድ

2. አራጣለ. ሀብታም ሆነ

3.ስውርሐ.ድብቅ

4.በለፀገመ.ምንም የለለው

5.አቋረጠሠ. ተወ

## አባሪ “5” የማስተማሪያ ጽሑፎች

**ትምህርት ሁለት፤የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

1 ባህል ማለት ምን ማለት ነው?

2 የሰቶችንና የባህልን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

3 በአከባቢያችሁ ሴቶችን የሚጎዱ ጎጂ ልማዶች አሉን?

4 ሴቶችን የሚጎዱ ልማዶችን ለማስወገድ መፍተሔው ምን ይመስላችኃል?

## ምንባብ

## “የሴቷ መንገድ”

ባህል ሰፍና ብዙ ጉዳዮችን የሚያካትት ማዕቀፍ ነው፡፡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ገጽታዎችም አሉት፡፡ባህል አንድ መህበራዊ ቡድን የሚገለገልባቸው ቁሶችን እንድሁም ማህበራዊ መተዳደሪያ ደንቦችን ያጠቃልላል፡፡በእነዚህም ውስጥ አስተሳሰቦችን፣ጥበቦችን፣ እምነቶችን፣ልማዶች ይነሳሉ፡፡እነዚህ በሰው ልጅ አከባቢያዊ እውቀት ላይ የተመሠረቱ ፈጠራዎች በዘልማድ በማህበረሰቡ እየተገበሩ ለዘናት ቆይተው የአኗኗር ዘይቤው ይሆናሉ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ለመልካም ብለው የሚተገሯችው ልማዳዊ ዲርጊቶች አንድአንድ ጊዜ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ሲያመዝን ይታያል፡፡በተለይ በሰቶች ላይ ስፈጸሙ የኖሩት አንድንድ ልማዳዊ ዲርግቶች ሴቶች ለረጅም ዘመናት የጨለማ ህይወትን እንድገፉ ያስገድዱ ነበር፡፡ለአብነትም ያህል የሴት ልጅ ብልት ትልተላ ፣ጠለፋ፣ የውርስ ጋብቻ፣ያለ እድሜ ጋብቻ፣ሴትን ልጅ በማጀት ውስጥ ብቻ ወስኖ መስቀመጥን---መጥቀስ ይቻላል፡፡እነዚህ ጎጂ ልማዶች ሴቶችን ለከፋ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት እየዳረጉ ዘመናትን አስቆጥረዋል፡፡የሚገርመው ግን ዲርግቶቹ ቀጣይነት እንዳይኖራቸውና ለትውልድ እንድተላለፋ የሴቶቹ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ሴቶቹ በባህል ስም የሚፈጸምባቸውን ጎጂ ዲርጊቶች በዝምታ ተቀብለውና ጉዳታቸውን በውስጣቸው አምቀው የዲርጊቶቹን አስፈላጊነት ለልጆቻቸው እየሰበኩ ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ያላቸውን ክብርና ታማኝነት ያሳያሉ፡፡ከዚህ በተቃራኒ እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ዲርጊቶች በመቃወም አንገታቸውን ቀና አድርገው ሽንጣቸውን ገትረው የመሚሚገቱ ጥቅት ደፋር ሴቶችም አልታጡም፡፡ወደዚህ አስቸጋሪና ውስብስብ ትግል ገብተው ድልን ከተቀዳጁ ጥቂት ጀግና ሴቶች መካከል የአንዷን ተሞክሮ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ "ሴት ልጅ አደባባይ ልትውል አይገባም" በሚባልበት ዘመን ተፈጥረው የባህሉን ጫና በጥረትና በትጋት አልፈው ለስኬት የበቁ ኢትዮጵያዊት ናቸው፡፡የእኚህ ጠንካራ ሴት መንገድ ምን ይመስል ነበር?

ቦጋለች (የአከባቢዋ ሰዎች እንደሚጠሯት ቦጌ) የተወለደችው ከአድስ አበባ 325 ኪ-ሜ በስተደቡብ ምዕራብ የከንባታ ጠንባሮ ዞን "ዛቶ" በተባለች ትንሽ መንደር ነው፡፡ቦጌ በተወለደችበት ዘመን በዛቶ የትኛዋም ሴት ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ አይፈቀድላትም፡፡ሴት ልጅ ከማጀት ጉዳዮች አልፋ ለትልቅ ቁምነገር ትደርሳለች ተብሎ በማህበረሰቡ አይታሰብም፡፡ይልቁንም ሴቶችን የሚጫኑ ልዩልዩ ጎጂ ልምዶች የሚከወኑበት በተለይ የሴት ልጅ ግርዛት በእጅጉ ተስፋፍቶ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡

የትንሽ ቦጌ መንገድ ግን የተለየ ነበር፡፡ ከቢጤዎቿ ፈጥና የነቃችው ቦጌ ወደ አጎቷ ቤት ጎራ እያለች ፍደል ከቆጠሩ ዘመዶቿ ማንበብና መጻፍ ቻለች፡፡የቤት ውስጥ ሥራዎች ካጠናቀቀች በኃላ ቤት ውስጥ ለምግብ ማብሰያ በሚቀጣጠለው እንጨት ብርሃን ሥራየ ብላ ጥናቷን ተያያዘችው፡፡ትጋቷን የተመለከቱ አባቷ ትምህርት ቤት እንድትሄድ ፈቀዱላት፡፡ በቀን እስከ 6 ማይል ርቀት በእግሯ እየተጓዘች ትምህርቷን ቀጠለች፡፡በግምት የዘጠኝ ዓመት ልጅ ስትሆን አራተኛ ክፍልን አጠናቅቃ ወደ አምስተኛ ክፍል ገባች፡፡ይህም በመንደሯ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአራተኛ ክፍል በላይ የደረሰች ሴት አደረጋት፡፡

በተማረቻት እውቀት ለአባቷና ለመንደሯ ሰዎች ማመልከቻ በመጻፍ በቀናነቷ የተመሰገነችና የታወቀች ሆነች፡፡ይህም አንድ ማዕረግ አሰጣት፡፡በከንባታ ባህል አባት ለክብሩ መገለጫ የሚጠራው በመጀመሪ ወንድ ልጁ ስሆን እናት የሚትጠራው ደግሞ በመጀመሪያ ሴት ልጇ ነበር፡፡ቦጌ ግን ነገሩን የተገላብጦሽ እንድሆን አደረገች፡፡የአከባቢው ሰው አባቷን በእሷ ስም "የቦጋለች አባት" እያለ መጥራት ጀመረ፡፡ቦጌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመቀጠል ወደ አድስ አበባ ከመጣች በኃላ በአገኘችው የነፃ ትምህርት እድል ወደ እስራኤል ሀገር ተጓዘች፡፡እስራኤል ሀገር ስትማር ከሚሰጣት የኪስ ገንዘብ በመቆተብም ወደ ሀገሯ ተመልሳ ለአባቷ በዛቶ መንደር የመጀመሪያ የተባለ የቆርቆሮ ቤት ሠራች፡፡ ቦጌ በአከባቢዋ አሁንም አስደናቂ የአስተሳሰብ ለውጥ እንድመጣ ምክንያት ሆነች፡፡ቤቱን ከሩቅም ከቅርብም ሰዎች እየመጡ ጎበኙት፡፡"ሴት ልጅ እድሉን ካገኘች ለካ ቁምነገር ትሰራለች" ተባለ፡፡ ቦጌ ባይጻፍም "ሴት ልጅ መደቧ ማጀት ነው"የሚለውን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከንባታ ወጣት ነች፡፡

ቦጌ በተሌ የውጭ ሀገራት በመዘዋወር ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታ "ኢፒዲሚዮሎጂ"በተባለ የትምህርት ዘርፍ የዶክትሬት ዲግሪዋን ተቀበለች፡፡ በውጭ ሀገራት ለ20 ዓመታት ከቆየች በኃላ በትውልድ አከባብዋ ያሉትን ሴቶች ለማገዝ በተለይ በሚፈጸምባቸው ባህላዊ ልማድ /ግርዛት/ሳቢያ በተለያ ሁኔታ በእጅጉ የሚጎዱ እህቶቿን ለመታደግ "ምናልባትም አንዲት ሴት ልጅ እንኳ ከግርዛት ባድን" በሚል ተስፋ ወደ ኢትዮጵያ ጠቅልላ መጣች፡፡እንዴ ኤ-አ በ1998 አከባቢ ከታናሽ እህቷ ፍቅርተ ገብሬ ጋር በመሆን "ከንባቲሜንቲ ጌዝማ-ቶጼ(ኬሜጌ)"የተባለ ገብረ ሰናይ ድርጅት አቋቋሙ ሴት ልጅን መግረዝ ቆሻሻማስወገድ ነው" ብሎፍጹም የሚያምነው የአከባብው ማህበረሰብ እምነት ጋርም ፍት ለፍት መጋፈጥ ጀመሩ፡፡ምንም እንኳ ፍቅርተ ገብሬ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት በአጭሩ መንገድ ላይ ብትቀርም ቦጌ የእህቷን አላማ ጭምር አንግባ ወደ ትግሉ ገባች፡፡ ትግሉ ቀላል አልነበረም፡፡ፍትም በመንደሯ ስሜ መልካም የነበረችው ቦጌ በትዕግስትና በዘዴ የአከባቢዋን ማህበረሰብ እሷ ወደምትፈልገው መንገድ ማስገባት ቻለች፡፡ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2008 ዓ-ም ተጠንቶ ይፋ በሆነው የዩኒሴፍ ጥናት በአከባቢው 97%(ፐርሰንት) ያህል ግርዛት መቀነሱ ተገልፀዋል፡፡

በተለያዩ በጎ አድራጎ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚደገፈው ከምባቲ ሜንቲ ጌዛማ -ቶጼ (ከሜጌ)ያገኘውን ድል በካምባታ አከባቢ ብቻ ባለመገደብ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡በእናቶች ጤና እና ስነ ተዋልዶ ፤በኤች አይ ቪ እና በአከባቢ ጥበቃ ዙርያ ማህበረሰቡን በማሳተፍ በርካታ ሽልማቶችንና ምስጋናን አትርፏል፡፡

ቁርጠኝንት የዓላማ ፅናት ለሌሎች በጎ ለማድረግ እውነተኛ ፍላጎት መኖር ይህችን ትንሽ ስራ ለወገኖቼ ለመሥራት አበቅቶኛል በሚሉት ጠንካራዋ ሴት በተለይ ሴቶችን ከተለያዩ የባህል ተፅዕኖዎች ለማውጣትና ጤናማና ነፃ ማህበረሰብ ለመገንባት፤እርስ በእርስ የሚከባበር፤የሚመካከር፤የሚማማር፤ሰላምና እኩልነትንየሚያስብ ዜጋ መፈጠር አለበት ይላሉ፡፡ይህ ደግሞ የሚሆነው ማህበረሰቡን በማዳመጥና በማስተማር ነው ብለውም ያምናሉ፡፡

የዶ/ር ቦጋለች መንገድ አባጣ ጎርባጣ ቢበዛውም በጽናት ይቀጥላል፡፡

(ምንጭ፤ "ከሜጌ" ቢሮ አድስ አበባ ቅርንጫፍ 2003 ዓ-ም)

**ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡**

1. በከምባታ ሴት ልጅ ትገረዝ የነበረው ምን በሚል ምክንያት ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

2.ትንሿቦጌ በአከባቢዋ ማህበረሰብ ዘንድ ሞገስ ያገኘችባቸውን ሁለቱን ዋናዋና ተግባራት ግለጹ?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

3. ዶ./ር ቦጋለች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ምን ተስፋ ሰንቀው ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

4.ሰላማዊ፤እኩልነትን የሚሻ ዜጋ ለማፍራት ዋናመሳሪያው ምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

5. ከዶ/ር ቦጋለች ህይወት ምን ተማራችሁ?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

6.ከምንባቡየተረዳችሁትን አሳጥራች በአንድ አንቀጽ ጻፋ?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

7. ቀደም ባሉት ጊዜት የከምባታ ሴት ወደ ትምህርት ቤት አንዳትሄድ የሚከለከለው ለምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

8. በዶ/ር ቦጋለች ጥረት በከንባታ አከባቢ የሴት ልጆች ግርዛት ምን ሁኔታ ላይ ደርሷል?

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

9. የዛቶ አከከባቢ ሰዎችን እጅግ ያስገረመው ምን ነበር?

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

10. የቦጌን የዓላማ ጽናትና ቀርጠኝነት ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን መልኩ አሳጥራችሁ ጻፉ?

…………………………………………………………………………………………………

…………………………………………………………………………………………………

## ትምህርት ሦስት አባሪ (6)፤ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሱስ ምንድን ነው?

2.የሱስን አስከፊ ገጽታ አጠር አድርጋችሁ ተናገሩ

## ምንባብ

### "የጉሌለው ሰካራም"

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማን ነው ብለው ገፈርሳ ደጅዝማች ይገዙ ሠፈር ለጠየቁ ሰዎች"ተበጀ" ሰካራሙ"ተበጀ!`"ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ነው! ብለው ይነግሯቸዋል፡፡

የህይወቱ ታሪክ ፍጹም ገድል ነው፡፡ ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው፡፡የራሱን ጠጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም፡፡ ማለዳ አይናገርም፣በጠርሙስ የሞላውን ከጠጣ በኋላ ማታ ስራገም ወይም ስሳደብ፣ስፎክር ወይም ስያቅራራ ድምጹ ከፈረንጁ ውሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ጋር ሁሉማታ ይስቃል፡፡የሰላምታው ዓይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው፡፡ከሰላምታ ጋር ድምጽ ትሰማላችሁ ከአፉ የሚወጣውን አንድ ቃል ግን መለየት አትችሉም፡፡

ተማሪዎች ከላይ ካነበባችሁት አንቀጽ ተበጀ ምን አይነት ሰው ነው? ማህበረሰቡስ ስለ እሱ ያለው አመለካከት ምን አይነት ይመስላችኋል?

ከሚያሰክር ሁሉ ለመታረም ብዙ ጊዜ አስቦ ነበር፡፡ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነበት ጊዜ "ከእንግዳ መጠጥ አልቀምስም" እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡በነጋታው የበለጠ ጠጥቶ የባስ ሰክሯል፡፡ለመስከር ይጠጣል፡፡ ደስ ያለው እንድመስለው ይጠጣል፡፡ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር መልኩን አይተው ያላወቁ ባልተቶች እንኳን በፍንጃል ቡናን ፉት እያሉ የሌላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ እያላከኩ ይሳሳቁበት ነበር፡፡ይህን መስከርህን ካልተውህ ላንተ ንሰሀ አባት አልሆንህም ብለው የመጀመሪያ ንሰሀ አባቱ ብዙከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከእርግማት ጋር አስወግደውታል፡፡ሠራተኞቹም ለእርሱ ተቀጥረው መሥራትን ከውርደት ቆጥረውት እየነቀፉት ሂደዋል፡፡ መጠጥ ካልተውክ አናገባህም ብለው በየጊዜው ለጋብቻ ጠይቋቸው

የነበሩ በቁመናው አሰናብተውታል፡፡በሰንቤተም፣ በማህበርም፣ ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን ሳይቀር ንቀውታል፡፡

ብዙ ጊዜ ሰክሮ አውቶሞቢል ሄዶበታል፡፡ሰክሮ በነጋታው ስነቃ እራሱን እስር ቤት ውስጥ አግኝቶታል፡፡ በጉለሌ መንገድ ዳር ባሉት የብዙ ውሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የጉለሌ ህዝብ አውቶታል፡፡ ሰክሮ የጎርፍ ውሃ ከወሰደው በኋላ ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል፡፡ ሰክሮ ከቤቱ መድረስ እያቃተው ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ፣ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ስሄድበበት አድሯል፡፡

ሰዎች መልካም የስማዕትነት ሥራውን ሁሉ ርካሽ አድርገው ይቆጥሩበታል፡፡በግብረገብ መሠረት አደረኩት የሚለውን ሁሉ በስካር እንዳደረገው ያናንቁበታል፡፡ በጎ ስራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አለበስከው፣አንተ ሰው ሰው ሁን ሚስት አግባ ልጆች ይኑሩህ ይሉና ይዘልፉት ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ውርደትና ርክሰት ነው እንጅ ክብር ከቶ አይደለም፡፡ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው፡፡ሰዎች ይሸሹታል፣ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናውን አይሹም፡፡እናም ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ ይሆናል፡፡የሰካራሙ ተበጀም እጣ ይሄው ነበር፡፡

ምንጭ፣(‹‹ተመስገን ገብሬ››፣የጉለሌው ሰካራም፣1941፣1-8 ለማስተማሪያ እንዲያመች ተሸሽሎ የቀረበ)

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ መልስ ስጡ፡፡

1. የጉለሌው ሰካራም ማን ነው?

………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………

2.የመጠጥ ሱስ በአቶ ተበጀ ላይ ያመጣው ባህር ምንድን ነው?

3. አቶ ተበጀን መጠጥ እንድያቆም የመከሩት ማን ናቸው? ምን ብለው መከሩት?

………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………

4. አቶ ተበጀን እንድናቅ ያደረገው ነገር ምንድን ነው እንዴት?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

5. የሱስን አስከፍነት አጠር አድርገህ ግለጽ?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

6.አቶ ተበጀን በቁመናው ያሰናበቱት ለምንድን ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

7. ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

8.አቶ ተበጀ በምን ዓይነት ሥራ ላይ ተሰማርቶ ይሠራ ነበር?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

9. ሱስ ያዋርዳል ሲል ምን ማለቱ ነው?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

10. የጉለሌውን ሰካራም አጭር ታሪክ በአንድ አንቀጽ ግለጽ?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

**ትምህርት አራት አባሪ (7)፤ የቅድሜ ምንባብ ጥያቄዎች**

1 ሥራና ምርት ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?

2 ጠንክሮ መሥራት ለራስ ፤ለሀገርና ለወገን ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?

**"የሥራ ያገኛል"**

ኢትዮጵያ በርካታ ህፃናትና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት፡፡እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፤አከባቢዎች፤ትምህርት ቤቶች፤ፖሊስ አውጭዎችና ፖለቲከኞች ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው፡፡ልጆች ትልልቅ ራዕይና ዓላማ እንዲዛዙ በቂ ችሎታና ሙያ እንድኖራቸው ከሁሉም በላይ ወላጆች ሀላፍነት አለባቸው፡፡ በሁሉም መስፈርቶች እያደገ የሚሄድ ቤተሰብ ሀላፍ የሆኑ ወላጆች ያሏቸው ልጆች ውስጣቸውን እየመረመሩ የቤቴሰባቸውን እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸው ምሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች ያሏቸው ልጆች ከወላጆቻቸው የበለጠ ባለ ራዕይ ይሆናሉ፡፡ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸውን ስያስተምሩ፤በህደት የእነርሱ ህይወት ከእለት ወደ እለት ለውጥ እያመጣ ሲሄድ፤በየበቤተሰቡ ያሉ አንድ ሁለት ሰው የራሴ የሚለው ሥራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፤ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው፡፡

አሁን አሁን እንደሚታየው ወላጆች በጣም ውስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸው፡፡የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ሁሉ ከቤቴሰብ አባላትና ከልጆች መኖር አለመኖር ጋር የሚያይዙ አሉ፡፡

በመሠረቱ ህፃናትወላጆቻቸውን አስገድደው የተወለዱ አይደሉም፤ህፃናትን የሚንወልዳቸው እኛ ነን፤በየትኞቹም ሀላፍነቶች በአብዛኛው ተጠያቂዎቹ እኛ ወላጆች ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል፡፡ኢትዮጵያ የሚታድገው እያንድንዱ ቤቴሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነው፡፡ወጣቱ አስተሳሰቡ ትኩስ ጉልበት አለው፤ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ አለው፤ፈጣን ነው፤አንድ ጊዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመሥራት ለማሸነፍ ሰፍ የእድሜ ገፀ-በረከት ያለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው፡፡ከማንም የተሻለ መኖር የሚፈልገው ወጣቱ ነው፡፡ይንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ መሥራት ያለበትም ወጣቱ ነው፡፡

በጥቂቶች የኢኮኖሚ ነፃ መውጣት ብዙ ሰው ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም፡፡የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም፤አትሆንም፡፡ ስለዚህ ሥራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድል ስላለው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ፍላጎትና ተነሳሽነትን እናስተምረው፡፡

ምንጭ፤ (ወሮታው በዛብህ፤ኢንተርፕረነርሽፕ፤1998፤109፤ለማስተማር እንድያመች ተደርጎ የተወሰደ፡፡)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ መልስ ስጡ፡፡**

1. ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው የተባሉትን አካላት በዝርዝር ጥቀሱ፡፡

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

2. ወጣቶች ሀገር ለመገንባት ቀዳሚ የህብረተሰቡ ክፍሎች ናቸው የተባሉበትን ምክንያት በዝርዝር አስረዱ፡፡

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

3. ቀና አስተሳሰብ ያላቸውን ልጆች ማፍራት የወላጆች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገልጧል፡፡ይህንን ሀሳብ ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት አስተያየት ጻፉ፡፡

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

4.“ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው” ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኃል?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

5. የወጣቶች በሀገር ግንባታ ዘርፍ ያላቸውን ሚና በአጭሩ ግለጽ?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

6. ወላጆች ለልጆቻቸው ማውረስ የሚገባቸውን ቀና አስተሳሰብ በዝርዝር ግለጽ?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

7. የሀገርንእድገት በተመለከተ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው ለምን?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

8. ቤቴሰብ ለልጆቹ ትንሹ ዩኒቨርሲቲ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

9. የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም ሲል ምን ማለቱ ነው?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

10. የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት (ጭብጥ) አሳጥረህ በአንድ አንቀጽ ጻፍ?

……………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………

አባሪ "8"፡- የቅድመ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት

| ኮድ | ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን ውጤት | | | | የቁጥጥር ቡድን ውጤት | | | |
| | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ |
| 1 | 46 | 46 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 2 | 46 | 45 | 47 | 46 | 43 | 45 | 45 | 44 |
| 3 | 44 | 45 | 43 | 44 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 4 | 46 | 45 | 44 | 45 | 45 | 44 | 43 | 44 |
| 5 | 45 | 43 | 44 | 44 | 45 | 43 | 44 | 44 |
| 6 | 46 | 44 | 45 | 45 | 47 | 45 | 46 | 46 |
| 7 | 46 | 45 | 47 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 8 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 9 | 48 | 45 | 45 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 10 | 44 | 45 | 46 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 11 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 47 | 46 | 46 |
| 12 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 13 | 45 | 44 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 14 | 48 | 45 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 15 | 42 | 40 | 44 | 42 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 16 | 47 | 43 | 45 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 17 | 48 | 45 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 18 | 46 | 46 | 43 | 45 | 44 | 43 | 45 | 44 |
| 19 | 48 | 43 | 44 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 20 | 43 | 45 | 44 | 44 | 46 | 47 | 45 | 46 |
| 21 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 22 | 43 | 45 | 44 | 44 | 42 | 45 | 42 | 43 |
| 23 | 44 | 46 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 24 | 48 | 44 | 43 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 25 | 44 | 45 | 43 | 44 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 26 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 27 | 42 | 44 | 43 | 43 | 44 | 43 | 42 | 43 |
| 28 | 44 | 45 | 43 | 44 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 29 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 30 | 44 | 44 | 44 | 44 | 44 | 43 | 42 | 43 |
| 31 | 43 | 44 | 45 | 44 | 42 | 44 | 46 | 44 |
| 32 | 48 | 43 | 44 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 |

አባሪ "9"፡- የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት

| ኮድ | ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን ውጤት | | | | የቁጥጥር ቡድን ውጤት | | | |
| | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ |
| 1 | 46 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 47 | 46 |
| 2 | 47 | 48 | 46 | 47 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 3 | 46 | 47 | 45 | 46 | 44 | 45 | 43 | 44 |
| 4 | 46 | 45 | 47 | 46 | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 5 | 46 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 6 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 7 | 47 | 45 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 8 | 46 | 45 | 47 | 46 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 9 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 10 | 46 | 44 | 48 | 46 | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 11 | 46 | 46 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 12 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 43 | 44 | 44 |
| 13 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 14 | 47 | 46 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 15 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 16 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 17 | 47 | 46 | 48 | 47 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 18 | 48 | 46 | 47 | 47 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 19 | 46 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 20 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 21 | 45 | 46 | 47 | 46 | 46 | 45 | 47 | 46 |
| 22 | 44 | 46 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 23 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 24 | 47 | 46 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 25 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 26 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 27 | 45 | 46 | 44 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 28 | 48 | 47 | 46 | 47 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 29 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 30 | 48 | 46 | 44 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 31 | 46 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 32 | 48 | 46 | 47 | 47 | 44 | 46 | 45 | 45 |

**አባሪ "10"፡- የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት**

| ኮድ | ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | | | | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | የቁጥጥር ቡድን | | | |
| | አራሚ.1 | አራሚ.2 | አራሚ.3 | አማካይ | አራሚ.1 | አራሚ.2 | አራሚ.3 | አማካይ | አራሚ.1 | አራሚ.2 | አራሚ.3 | አማካይ | አራሚ.1 | አራሚ.2 | አራሚ.3 | አማካይ |
| 1 | 46 | 46 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 | 46 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 47 | 46 |
| 2 | 46 | 45 | 47 | 46 | 43 | 45 | 45 | 44 | 47 | 48 | 46 | 47 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 3 | 44 | 45 | 43 | 44 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 47 | 45 | 46 | 44 | 45 | 43 | 44 |
| 4 | 46 | 45 | 44 | 45 | 45 | 44 | 43 | 44 | 46 | 45 | 47 | 46 | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 5 | 45 | 43 | 44 | 44 | 45 | 43 | 44 | 44 | 46 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 6 | 46 | 44 | 45 | 45 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 7 | 46 | 45 | 47 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 | 47 | 45 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 8 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 45 | 47 | 46 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 9 | 48 | 45 | 45 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 10 | 44 | 45 | 46 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 44 | 48 | 46 | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 11 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 47 | 46 | 46 | 46 | 46 | 46 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 12 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 43 | 44 | 44 |
| 13 | 45 | 44 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 14 | 48 | 45 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 47 | 46 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 15 | 42 | 40 | 44 | 42 | 46 | 44 | 45 | 45 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 16 | 47 | 43 | 45 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 17 | 48 | 45 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 | 47 | 46 | 48 | 47 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 18 | 46 | 46 | 43 | 45 | 44 | 43 | 45 | 44 | 48 | 46 | 47 | 47 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 19 | 48 | 43 | 44 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 47 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 20 | 43 | 45 | 44 | 44 | 46 | 47 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 21 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 47 | 46 | 46 | 45 | 47 | 46 |
| 22 | 43 | 45 | 44 | 44 | 42 | 45 | 42 | 43 | 44 | 46 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 | 45 |
| 23 | 44 | 46 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 24 | 48 | 44 | 43 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 | 47 | 46 | 45 | 46 | 46 | 45 | 44 | 45 |
| 25 | 44 | 45 | 43 | 44 | 44 | 45 | 46 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 |
| 26 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 27 | 42 | 44 | 43 | 43 | 44 | 43 | 42 | 43 | 45 | 46 | 44 | 45 | 44 | 45 | 46 | 45 |
| 28 | 44 | 45 | 43 | 44 | 45 | 45 | 45 | 45 | 48 | 47 | 46 | 47 | 46 | 46 | 46 | 46 |
| 29 | 45 | 45 | 45 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 30 | 44 | 44 | 44 | 44 | 44 | 43 | 42 | 43 | 48 | 46 | 44 | 46 | 45 | 46 | 44 | 45 |
| 31 | 43 | 44 | 45 | 44 | 42 | 44 | 46 | 44 | 46 | 46 | 46 | 46 | 46 | 44 | 45 | 45 |
| 32 | 48 | 43 | 44 | 45 | 45 | 46 | 44 | 45 | 48 | 46 | 47 | 47 | 44 | 46 | 45 | 45 |